EVERY CHILD READY @Home

ክፍል 11

የአካል ብቃት በመስራት መዝናናት

PK3

AppleTree

ክፍል 11
የአካል ብቃት በመስራት መዝናናት

©2021
ሁሉም መብቶች በሕግ የተጠበቁ ናቸዉ። በዚህ የቅጂ መብት ስር ከለላ የተደረገላቸዉን መብቶች ላይ ገደብ ሳያስቀምጥ፣ የዚህ ህትመት የትኛዉም አካል ማባዛት አይቻልም፣ ማከማቸት፣ ወይም በድጋሚ ጥቅም ላይ የሚያዉል ስርዓት ዉስጥ ሊካተት አይችልም፣ ወይም በማንኛዉም መልክ ወይም ሁኔታ(ኤለክትሮኒክ፣ ሜካኒካል፣ ፎቶኮፒ፣ ድምጽ ቅጂ፣ ወይም ሌላ መንገድ) ቀደም ብሎ ከተሰጠ የጽሁፍ ፍቃድ ዉጪ ማስተላለፍ አይቻልም።

አፕል ትሪ ኢንቲቲዩት ፎር ኤዱኬሽን ኤኖቬሽን
1801 ሚሲሲፒ ጎዳና ኤስኢ፣ 3ኛ ፎቅ
ዋሽንግተን፣ ዲሲ 20020

የቅጂ መብት ©2021 ጽሁፍ እና የምስል ገለጻዎች። አፕል ትሪ ኢንስቲቲዩት። ሁሉም መብቶች በህግ የተጠበቁ ናቸዉ።

የPK3 ክፍል 11 ሳምንት 1 ጠቅላላ ምልከታ

ውድ ቤተሰቦች፡

የአካል ብቃት በመስራት ለመዝናናት፣ በእንቅስቃሴና የልጅዎና የቤተሰብዎ የበጋ ወቅት መዝናኛ ላይ ትኩረት ለሚያደርግ ክፍል ይዘጋጁ።

ክፍል 11 መጻህፍት

- *የአይሳቤል የስጦታ እቃ መያዣ/Isabel's Treasure Tub* በ Ruth Ebisuzaki
- *ወደ ውጭ ወጥቶ መጫወት/Go Outside and Play* በ Felicia R. Truong
- *ማክሲሚሊያን/Maximilian፣ ትልቁ የአለማችን እጅግ ድንቅ የምግብ ባለሙያ/The Greatest Most Extraordinary Chef in the World* በ Felicia R. Truong
- *የተረጋጋ ሰውነት መጽሀፍ/The Calm Body Book* በ Phoenix Lynn Minklei Fermin

ECR@ የቤት ውስጥ ተግባሮች/ECR@ Home Activities ስለ ከቤት ውጭና የቤት ውስጥ የስፖርትና የአካል እንቅስቃሴዎች፣ ጥሩ ተጫዋች መሆን እና ሰውነት ለማረጋጋት የተለያዩ ስትራቴጂዎችን መጠቀም የተመለከተ ትምህርት ይይዛል። ልጅዎ በተጨማሪም እራሱን ስለሚንከባከብባቸውና ደህንነቱን ስለሚጠብቅባቸው ዘዴዎች ይማራል፤ መስመሮች መሳል፣ መቁጠር እና ቃላት ለመመስረት የቃላት ድምጾችን መቀላቀል ይለማመዳል።

ክፍል 11 ቃላት

- መረጋጋት
- የአካል ብቃት መስራት
- ጤናማነት
- የደህንነት መጠበቅ
- የስፖርት አይነቶች
- የበጋ ወቅት
- ቡድን
- የቡድን አጋር
- የክረምት ወቅት

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ሳምንት 1

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

የPK3 ክፍል 11 ሳምንት 1 ጠቅላላ ምልከታ

የቤት ውስጥ አካል ብቃት

በዚህ ሳምንት ልጅዎ፥

በዚህ ሳምንት ልጅዎ በቤት ውስጥ አካል ብቃት ላይ ትኩረት ያደርጋል። ልጅዎ በሚደንስበት ወቅት መመሪያዎችን መከተል፣ ስታዲየም መገንባት/መስራት፣ እንቅስቃሴውን መመዝገብ እና በቡድን መመደብ ይለማመዳል። እነዚህን ተግባሮች በቤትዎ ውስጥ ከልጅዎ ጋር አብረው በመጫወት ማስፋፋጥ ይችላሉ። በምትጫወቱበት ወቅት የተለያዩ ቁሶችን በቡድን በመመደብ ወይም በምትደንሱበት ወቅት ስብስብ በመስራት ተዝናኑ።

ቁልፍ ቃላት

እንቅስቃሴ

የሰውነታችንን ጤናና ጥንካሬ ለመጠበቅ የምናደርጋቸው ነገሮች

የስፖርት አይነቶች

ሰዎች እርስ በርሳቸው የሚፎካከሩባቸው ተግባሮች

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

በዚህ ሳምንት ስለ እንቅስቃሴና የስፖርት አይነቶች ትማራላችሁ። መርሀ ግብሩን ከመጀመራችሁ በፊት ስለሚወዱት እንቅስቃሴ ይጻፉ እንዲሁም ይሳሉ።

ያስቡበት!

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ሰኞ

PK3 ክፍል 11 ሳምንት 1 ቀን 1

STEM: በቀለም መመደብ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ በቤትዎ ውስጥ የሚገኙ ቀይ፣ ቢጫና ሰማያዊ ቁሶች

- ለልጅዎ እያንዳንዱን ቁስ ያሳዩት። ከዚያም **እነዚህን ቁሶች እንዴት በቡድን መመደብ እንችላለን?** ብለው ይጠይቁት።
- ከዚያም **እስኪ ተመሳሳይ ቀለም ያላቸው ቁሶችን በቡድን እንመድብ ወይም አንድ ላይ እናድርጋቸው** ብለው ይንገሩት።
- አንድ ላይ ሆናችሁ የቀይ፣ ቢጫና ሰማያዊ ምድብ ስሩ።
- በተጨማሪም ልጅዎ የሚነግሩዎትን ቀለሞች ሊጨምሩ ወይም ቁሶችን ልጅዎ በሚነግርዎ በሌላ ዘዴ ለምሳሌ፡ በመጠን አንድ ላይ መመደብ ትችላላችሁ።

በግል መማር፥ የስፖርት እቃዎች

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለሮች፣ [የስፖርት እቃዎች ቀለም መቀቢያ]



- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው እንዴት እንደ እግር ኳስ የመሳሰሉ ስፖርቶችን እንደምትጫወቱ እና እንዴት እንደ ቴኒስ ራኬት የመሳሰሉ የተለያዩ ቁሶችን እንደምትጠቀሙ ተነጋገሩ።
- ለጅዎን እራሱን ችሎ የተለያዩ የስፖርት እቃዎችን እንዲቀባ ያድርጉ።
- ቀጥለውም **ኳስ የምንጠቀምበትን ስፖርት ስም ልትነግረኝ ትችላለህ? የትኛውን ስፖርት መሞከር ትፈልጋለህ?** ብለው ይጠይቁት።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ሰኞ

እውቀት፥ የዳንስ እንቅስቃሴዎች

- ከልጅዎ ጋር እንደ ሆኪ ፖኪ የመሳሰለ ዳንስ በጋራ ለማየት ስልክ ወይም ታብሌት ይጠቀሙ።
- ከዚያም **ሁለት የዳንስ እንቅስቃሴዎችን እንድትሰራ እጠይቅሀለሁ** ይበሉት። ሁለት የዳንስ እንቅስቃሴዎች ይጠቀሙት፤ ለምሳሌ፡ መዟዟርና መንሸራተት
- ባለ ሁለት ደረጃ እንቅስቃሴዎችን በመስጠትዎ ይቀጥሉ።
- ሚናችሁን ተቀያየሩና ለልጅዎ እንቅስቃሴዎቹን እንዲጠቁም ይፍቀዱለት።

ያንብቡ፥ የአይሳቤል የስጦታ እቃ መያዣ/*Isabel's Treasure Tub*

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ [*የአይሳቤል የስጦታ እቃ መያዣ/Isabel's Treasure Tub*], **የእቃ መያዣ**

- ምንባቡን ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ያንብቡ።
- ከዚያም በቤታችሁ ውስጥ የየራሳችሁን ስጦታ ፈልጉ። ልጅዎን ለሱ ልዩ ቦታ ያለቻውን ቁሶች እንዲፈልግ ይፍቀዱለት ወይም ልዩ ቁሶችን እንዲፈልግ ይጠይቁት፤ ለምሳሌ፡ ቀይ ወይም ቢጫ ከለር ያላቸው ቁሶች፣ ወይም ለማድ ቤት የሚያገለግሉ ቁሶች።
- ቀጥሎም ልጅዎን ሁሉንም ቀይ ቀለም ያላቸው ቁሶችን አንድ ላይ እና ቢጫ ቀለም ያላቸው ቁሶችን በሌላ ምድብ አንድ ላይ ወይም የማድ ቤት ቁሶችን በአገልግሎታቸው አንድ ላይ በመመደብ (ምሳ፡ ለመብላትና ለመጠጣት የምንጠቀምባቸው ቁሶች እና የምናበስልባቸው ቁሶች) ቁሶቹን በቡድን እንዲመድብ ያበረታቱት።

በተጨማሪም የአይሳቤል የስጦታ እቃ መያዣ/Isabel's Treasure Tub በቅድሚያ የተቀዳ ምንባብን ከዩቲዩብ *ሁሌንም ህጻናት ዝግጁ ማድረግ ቻነል/ Every Child Ready* YouTube channel ላይ ማግኘት ትችላላችሁ።

የአይሳቤል የስጦታ እቃ መያዣ



ሩት ኢብሱዛኪ ሰዓሊ፥ ፔጊ ፓሬድስ ሪክስ

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ቤዝቦል

ቤዝቦል

የቤዝቦል ጓንት



የቤዝቦል ዱላ/ባት

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

እግር ኳስ

ኳስ



የእግር ኳስ መረብ

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ቴኒስ

የቴኒስ ኳስ

የቴኒስ ራኬት

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ቅርጫት ኳስ



የቅርጫት ኳስ

የቅርጫት ኳስ መረብ

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ማክሰኞ

PK3 ክፍል 11 ሳምንት 1 ቀን 2

STEM: የስታዲየም ሞዴል ዲዛይን ማዘጋጀት

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ [ስታዲየሞች፣](#) ወረቀት፣ ከለሮች፣ ማጣበቂያ፣ መቀስ፣ ካርቶን፣ *በአማታጭነት - ተጨማሪ ንጹህ በድጋሚ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሶች*

- ከልጅዎ ጋር ሆነው የተለያዩ ስፖርቶች ስታዲየሞች ስዕሎችን ይመልከቱ።
- ቁሶቹን ለልጅዎ ያሳዩት። ከዚያም ስታዲየም ለመገንባት መጠቀም ስለሚችላቸው ቁሶች ይንገሩት።
- አንድ ላይ ሆናችሁ የስፖርቶች ስታዲየም መገንቢያ ዲዛይን ጻፉ እንዲሁም ሳሉ። ከዚያም **ስለ ስታዲየም ልትነግረኝ ትችላለህ? በስታዲየሞች ውስጥ የምን አይነት ስፖርቶች ጨዋታ ይካሄዳል?** ብለው ይጠይቁት።
- ከዚያም በዚህ ሳምንት በቀጣይ ስታዲየም እንደሚገነባ/እንደሚሰራ ይንገሩት።



በግል መማር፡ ምት መምረጥ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ሙዚቃ፣ ወረቀት፣ ከለሮች

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው የምታዳምጡት ከፍ ያለ ምት ያለው ሙዚቃ ምረጡ። ምቱን መፈለግ ለመለማመድ አጨብጭቡ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ የሙዚቃውን ምት እንዲስልና እንዲቀባ ያድርጉ። የተሞነጫጨረ ስዕል ቢስልም ምንም ማለት አይደለም!
- ከዚያም **ስለ ስዕልህ ልትነግረኝ ትችላለህ? ስዕሉ የሙዚቃውን ምት የሚያሳየው እንዴት ነው?** ብለው ይጠይቁት።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ማክሰኞ

PK3 ክፍል 11 ሳምንት 1 ቀን 2

እውቀት፥ እስኪ እንለማመድ

- ልጅዎን **ሁለት የእንቅስቃሴ ሙከራዎች እንድትሰራ እጠይቅሀለሁ** ይበሉት። ለልጅዎ ሁለት የእንቅስቃሴ ሙከራዎችን ይንገሩት፤ ለምሳሌ፡ 2 ጃኮችን ዝለል ወይም ቁጢጥ በልና ከዚያም ዝለል።
- ባለ ሁለት ደረጃ ሙከራዎች መስጠትዎን ይቀጥሉ።
- ሚናችሁን ተቀያየሩ። ልጅዎ ሁለት የእንቅስቃሴ ሙከራዎች ይነግርዎና እርስዎ የሚሰጥዎትን መመሪያዎች ይከተላሉ።
- ሶስት የእንቅስቃሴ ሙከራዎችን በመጠቀም ይህን ተግባር ማስፋፋት ይችላሉ።

የጆርናል ሙከራ፥ የቤት ውስጥ መዝናኛ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለሮች፣ የቤት ውስጥ መዝናኛ

- ከልጅዎ ጋር በቤት ውስጥ መጫወት ስለሚወድባቸው ዘዴዎች ይነጋገሩ።
- ልጅዎን ስለእነዚህ ዘዴዎች እንዲጽፍና እንዲስል ያድርጉ።
- ከዚያም **በቤት ውስጥ ምን ማድረግ ትወዳለህ? ይህን ማድረግ የሚያስደስትህ ለምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ ________________

በቤት ውስጥ ምን ምን ነገሮችን መስራት ያስደስታችኋል?

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ረቡዕ

STEM: በቅርጽ መመደብ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለሮች፣ ቅርጾች

- ለልጅዎ እያንዳንዱን ቅርጾች ያሳዩት። ከዚያም **እነዚህን ቁሶች እንዴት በቡድን መመደብ እንችላለን?** ብለው ይጠይቁት።
- ከዚያም **እስኪ ተመሳሳይ ቅርጽ ያላቸውን ነገሮች በቡድን እንመድብ ወይም አንድ ላይ እናድርጋቸው** ብለው ይንገሩት።
- አንድ ላይ ሆናችሁ የሶስት ማዕዘኖች፣ የክቦችና አራት ማዕዘኖች ምድብ ስሩ።
- ልጅዎ በተጨማሪም በምድቦቹ ውስጥ የሚጨምራቸው ተመሳሳይ ቅርጽ ያላቸው የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን ሊፈልግ ይችላል።



በግል መማር፥ የሙከራ ጆርናሌ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለሮች፣ የሙከራ ጆርናል

- ሁለት ገጾችን አንድ ላይ አድርገው እኩል ቦታ በማጠፍ ደብተር ይስሩ።
- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስለ ሙከራ አይነቶችና ለምን እንደሚያስፈልጉ ተነጋገሩ።
- ልጅዎ እራሱን ችሎ የመጽሀፉን የሽፋን ገጽ እንዲስል ያድርጉ። ልጅዎ በተጨማሪም እራሱን ችሎ ስለ ሙከራ ሊጽፍና ሊስል ይችላል፤ ለምሳሌ፡ የሚወደው ሙከራ ወይም በዛ ቀን በገጽ 1 ላይ ስለሰራው ሙከራ።
- ቀጥለውም **የዛሬውን ሙከራህን እንዴት ሰራኸው?** ብለው ይጠይቁት።

ጆርናሉን በዚህ ሳምንት በቀጣይ ለመጠቀም ያስቀምጡት።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ረቡዕ

እውቀት፥ መስመሮች መሳል

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለሮች፣ ወረቀት፣ መስመሮች

- ልጅዎን እራሱን ችሎ የተሰጠውን ገጽ በመጠቀም የቁመትና የአግድመት መስመሮችን ፈልጎ እንዲያገኝ ያድርጉ።
- ልጅዎ በተጨማሪም ያለ ፍለጋ ባዶ ቁራጭ ወረቀት በመጠቀም የቁመትና የአገድመት መስመሮች ሊስል ይችላል።



ያንብቡ፥ የአይሳቤል የስጦታ እቃ መያዣ/*Isabel's Treasure Tub*

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ *የአይሳቤል የስጦታ እቃ መያዣ/Isabel's Treasure Tub*፣ ብዙ የተለያየ መጠን ያላቸው ቁሶች።

- ከልጅዎ ጋር መጽሀፉን አብረው ያንብቡ።
- ካነበባችሁ በኋላ ቁሶችን በመጠናቸው አንድ ላይ መመደብ ተለማመዱ። ለልጅዎ **እስኪ መጠናቸው አንድ አይነት የሆኑ ነገሮችን እናቧድን ወይም አንድ ላይ እንመድብ** ብለው ይንገሩት።
- የትናንሽና የትላልቅ ቁሶች ምድብ ስሩ። በተጨማሪም ቁሶችን በቀለማቸው፣ ቅርጻቸው፣ ወዘተ መመደብ ልትለማመዱ ትችላላችሁ።

የአይሳቤል የስጦታ እቃ መያዣ



ሩት ኢብሱዛኪ ሰዓሊ፥ ፔጊ ፓሬድስ ሪክስ

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ረቡዕ

እስኪ እንንቀሳቀስ፥ መቆም መደነስ እና መከተል

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ሙዚቃ

- ለልጅዎ **አሁን መቆም መደነስና መከተል ተብሎ የሚጠራ ጌም እንጫወታለን ሙዚቃውን ስትሰማ መደነስ ትችላለህ። ሙዚቃው ሲያቆም ቀጥ ብለህ ትቆምና የምሰጥህን መመሪያ ትከተላለህ** ብለው ይንገሩት።
- ከልጅዎ ጋር አብረው ይደንሱ። ሙዚቃውን ያቁሙ፣ ቀጥ ብላችሁ ቁሙና እንደ አፍንጫህን ንካ የመሳሰሉ መመሪያዎች ይስጡት።
- ተራና መመሪያ መስጠት እየተቀያየራችሁ ሙከራውን ብዙ ጊዜ ደጋግማችሁ ስሩ።

አንድ ላይ ሆኖ መማር፥ የስጦታ ፍለጋ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ እንደ ስጦታ የሚያገለግሉ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች ወይም አሻንጉሊቶች፣ *በአማራጭነት - ወረቀት፣ ከለሮች*

- እርስዎ ተመሳሳዩን በሚያደርጉበት ወቅት ልጅዎን ለስጦታ ፍለጋ የተወሰኑ ቁሶችን እንዲደብቅ ይፍቀዱለት።
- አንድ ላይ ሆናችሁ ለስጦታ ፍለጋ እንዲረዳችሁ ቀላል ካርታ ልታዘጋጁ ትችላላችሁ ወይም ወደ ስጦታ ፍለጋ በምትሄዱበት ወቅት አንዳችሁ ለሌላችሁ ፍንጭ ልትሰጡ ትችላላችሁ።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።








©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

የአካል ብቃት እንቅስቃሴዬ ጆርናል

ስም፡ ______________________

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፦ ____________

ስም፦ ____________

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም ____________



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ሃሙስ

STEM: የስታዲየም ሞዴል መገንባት/መስራት

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ወረቀት፣ ከለሮች፣ ማጣበቂያ፣ መቀስ፣ ካርቶን፣ በቀን 17 የተሰራ ዲዛይን፣ *በአማራጭነት - ንጹህ በድጋሚ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሶች*

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው በዚህ ሳምንት ቀደም ብሎ የሰራውን ዲዛይን ተመልከቱ። የግንባታ እቃዎችን ለልጅዎ ያሳዩት።
- አንድ ላይ ሆናችሁ እቃዎቹን ስታዲየም ለመገንባት/ለመስራት ተጠቀሙባቸው። እየሰራችሁ ተነጋገሩ። **የስታዲየም ግንባታችንን እንዴት ልንጀምር እንችላለን? ይህን እቃ እዚህ ጋር የተጠቀምከው ለምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት።
- ልጅዎን ስለ ጥረቱ ያመስግኑት እና ስታዲየሙ ቢወድቅ ወይም የጠበቀውን አይነት ባይመስልም ምንም ማለት እንዳልሆነ ያስታውሱት!

በግል መማር፡ በጥበብ የተደረደሩ ድንጋዮችን ቀለም መቀባት

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ወረቀት፣ ከለሮች፣ [Tessellations/በጥበብ የተደረደሩ ድንጋዮች]

- ለልጅዎ **በጥበብ የተደረደሩ ድንጋዮች የተለያዩ ቅርጾች ያሏቸው በጥበብ የተደረደሩ ድንጋዮች ሲሆኑ በአብዛኛው ፓተርን ይሰራሉ** በለው ይንገሩት።
- ልጅዎን አራሱን ችሎ ቅርጾቹን እንዲቀባ ያድርጉ። ልጅዎን እንደ ቀይ -ሰማያዊ-ቀይ-ሰማያዊ-ቀይ ሰማያዊ የመሳሰሉ ፓተርኖችን እንዲቀባ ያበረታቱት።
- ቀጥለውም ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ቅርጾቹን ለዩና ጎኖቹና ማዕዘኖቹን በመቁጠር ስለ ቅርጹ ባህሪያት ተነጋገሩ።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ሃሙስ

PK3 ክፍል 11 ሳምንት 1 ቀን 4

እውቀት፥ የቃላት ድምጾችን መቀላቀል

- ለልጅዎ **እስኪ ቃላትን እንቀላቅል! የዚህን ቃል የመጀመሪያ ድምጽና ቀሪ ድምጾችን እቀላቅላለሁ። J-og፣ j-og** ብለው ይንገሩት። ሁለቱ ክፍሎችን አንድ ላይ በሚቀላቅሉበት ወቅት በፍጥነት ይድገሙ። **J-og፣ jog። አሁን አንተ ትሞክራለህ j-og, jog!**
- **አሁን የአንተ ተራ ነው!** ይበሉተ። r-un (run)፣ h-op (hop)፣ እና j-ump (jump) የሚሉት ቃላተን ይጠቀሙ።

የጆርናል ሙከራ፥ የምወደው ስፖርት

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለሮች፣ የምወደው ስፖርት

ስም፡ ________________
ስለምትወዱት የስፖርት አይነት ጻፉ እንዲሁም ስዕል ሳሉ።

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ከስልክዎ ወይም ታብሌትዎ ላይ ስለተለያዩ ስፖርቶች እየተነጋገራችሁ ስዕሎች ተመልከቱ።
- ልጅዎ እራሱን ችሎ ስለ ስፖርት አይነቱ እንዲጽፍና እንዲስል ያድርጉ።
- ከዚያም **የምትወደው ስፖርት ምንድን ነው? ይህን ስፖርት ለምን ወደድከው?** ብለው ይጠይቁት።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ ________________

ስለምትወዱት የስፖርት አይነት ጻፉ እንዲሁም ስዕል ሳሉ።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

አርብ

STEM: ስብስቦችን መቁጠር

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የወረቀት ሰሌዳ፣ ከለሮች ወይም ሌሎች ትናንሽ ቁሶች

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስብስቦችን መስራት ተለማመዱ። ከዚያም **እኔ ቁጥር እጠራለሁ። አንተ ስብስቡን ወይም የነገሮች ምድብን ሰሌዳው ላይ ታስቀምጣለህ** ብለው ይንገሩት።
- ሶስት አይነት ከለሮች በወረቀት ሰሌዳው ላይ ያስቀምጡ። **ይህ የሶስት ነገሮች ስብስብ ነው! እስኪ እንቁጠራቸው፤ 1, 2, 3!** ይበሉት።
- **አሁን የአንተ ተራ ነው! የአምስት ነገሮች ስብስብ ትሰራለህ!** ይበሉት።
- ልጅዎን እስከ 10 ቁሶች ስብስብ እንዲሰራና ቁሶቹን እንዲቆጥር ያድርጉት።
- ይህን ተግባር ያስፋፉ: የቁጥር ካርዶች ያዘጋጁና ልጅዎን ቁጥር መርጦ ከቁጥሩ ጋር የሚዛመድ ስብስብ እንዲሰራ ያድርጉ።

በግል መማር፥ የእንቅስቃሴ ሙከራ ጆርናሌ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የቀን 3 የሙከራ ጆርናል፣ ከለሮች



- ከልጅዎ ጋር በዚህ ሳምንት ስለሰራቸው የእንቅስቃሴዎች ሙከራዎች ይነጋገሩ።
- ልጃዎን እራሱን ችሎ ስለ እንቅስቃሴ ሙከራው በገጽ 2 ላይ እንዲጽፍና እንዲስል ያድርጉ።
- ልጅዎን ለመጽሀፉ የጀርባ ገጽ እንዲስል ያድርጉ።
- ቀጥለውም **ይህ እንቅስቃሴ የሚያስፈልገው ለምንድን ነው? ይህ እንቅስቃሴ የሰውነትህን ጤና የሚጠብቀው እንዴት ነው?** ብለው ይጠይቁት።

ልጅዎ በዚህ ክፍል ውስጥ በሙሉ እንደ አስፈላጊነቱ ገጾችን በመጨመር ይህን የእንቅስቃሴ ሙከራ ጆረናል መጠቀሙን ሊቀጥል ይችላል።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

አርብ

እውቀት፡ ስለ ቃላት መግለጽ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ በቤትዎ ውስጥ የሚገኙ የተለያየ ውፍረት ያላቸው ቁሶች

- ለልጅዎ ቁሶቹን ያሳዩት። ከዚያም ሸካራና ለስላሳ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይንገሩት።
- አንድ ላይ ሆናችሁ የቁሱን ልስላሴ በመዳሰስ ለዩ እና ሻካራ ወይም ለስላሳ ስለመሆኑ ግለጹ። ለጀዎን **ይህ** ___(ቁስ)___ **የ** ___(ሸካራነት/ለስላሳነት)___ ስሜት ጥሰጣል ብሎ እንዲናገር ያበረታቱት።
- በተጨማሪም ስለ መጠን፣ ቅርጽ፣ ቀለም ወይም ባህሪያት ልትገልጹ ትችላላችሁ።

ያንብቡ፡ የአይሳቤል የስጦታ እቃ መያዣ/Isabel's Treasure Tub

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ *[የአይሳቤል የስጦታ እቃ መያዣ/Isabel's Treasure Tub]*፣ **2 የእቃ መያዣዎች፣ እንደ አሻንጉሊቶችና መጽሀፎች የመሳሰሉ ቁሳቁሶች**

- ምንባቡን ከልጅዎ ጋር ሆነው ያንብቡ።
- ከዚያም ልጅዎን ነገሮችን በቡድን እየመደበ በማጽዳትና ከዚያም እያስወገደ በሚማርበት ወቅት (ለምሳሌ፡ አሻንጉሊቶቹን በአንድ እቃ መያዣና መጽሀፎቹን በሌላ እቃ መያዣ) በቡድን መመደብ እንዲለማመድ ያበረታቱት።
- ልጅዎን የእቃ መያዣዎቹን እንዲያስውብ በማድረግ ወይም ቁሶችን በቡድን የሚመድብባቸውና የሚያስወግድባቸው ሌሎች ቦታዎችን በማሳየት ይህን ተግባር ያስፋፉ (ለምሳሌ፡ ልጅዎን ልብሶቹን፣ አሻንጉሊቶቹን እና ጫማዎቹን ለያይቶ ማስቀመጥ እንዲማር በመርዳት)።

የአይሳቤል የስጦታ እቃ መያዣ



ሩት ኢብሱዛኪ ሰዓሊ፡ ፔጊ ፓሬድስ ሪክስ

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ሳምንት 2

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

የPK3 ክፍል 11 ሳምንት 2 ጠቅላላ ምልከታ

ከቤት ውጭ የሚሰራ የአካል ብቃት

በዚህ ሳምንት ልጅዎ፥

በዚህ ሳምንት ልጅዎ ከቤት ውጭ በሚሰራ የአካል ብቃት ላይ ትኩረት ያደርጋል እንዲሁም ስለ በጋ ወቅት እና የክረምት ወቅት ስፖርቶች ይማራል። ልጅዎ ዛይሎፎን ይሰራል፣ የመጽሀፉን ክፍሎች ያጠናል፣ መስመሮች መሳል ይለማመዳል እንዲሁም እየቆጠረ እንቅስቃሴ ይሰራል። ከልጅዎ ጋር ሆነው በምትቆጥሩበት ወይም የምትወዱትን ስፖርት በምትጫወቱበት ወቅት እንቅስቃሴ በመስራትና ወደ ውጭ በመውጣት ትዝናናላችሁ።

ቁልፍ ቃላት

የስፖርት አይነቶች
ሰዎች እርስ በርሳቸው የሚፎካከሩባቸው ተግባሮች

የበጋ ወቅት
የአመቱ ሞቃት ወቅት ነው።

የክረምት ወቅት
የአመቱ ቀዝቃዛ ወቅት ነው።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

በዚህ ሳምንት እንደ በረዶ መንሸራተት ወይም ሸርተቴ ስለመሳሰሉ ስፖርቶች ትማራላችሁ። መርሀግብሩን ከመጀመርዎ በፊት በቀዝቃዛ ወቅት ወደ ውጭ ሲወጡ ማድረግ ስለሚወዷቸው ነገሮች ይጻፉ እንዲሁም ይሳሉ።

ያስቡበት!

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ሰኞ

STEM: ቁጢጥ ማለት

- ከእንቅስቃሴ ሙከራዎች ጋር እስከ 10 መቁጠር ተለማመዱ።
- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው 8 ቁጢጥ ማለቶችን ሞክሩ። ቁጢጥ ማለት ያሳዩት። በትከሻዎ ትይዩ በእግርዎ ቀጥ ብለው ይቁሙ። ልክ ወንበር ላይ እንደሚቀመጡ አይነት እስከ ጉልበትዎና ታፋዎ ድረስ ያጎንብሱ። ተመልሰው ይቁሙና 1 ብለው ይቁጠሩ። በተለያዩ ብዛቶች ቁጢጥ ማለት፣ መቁጠር ይቀጥሉ።
- ልጅዎ ዘግጁ ከሆነ ከ10 በላይ ቁጠሩ።

በግል መማር፥ የበጋ ወቅት ስፖርቶች

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለሮች፣ ወረቀት፣ [የበጋ ወቅት ስፖርቶች]

- ከልጅዎ ጋር እንደ መንሸራተት፣ አስመስሎ መንሸራተት ወይም ቦብስሌዲንግ ስለመሳሰሉ የተለያዩ የበጋ ወቅት ስፖርቶች ተነጋገሩ። ለስፖርቶቹ የሚያስፈልገውን መሳሪያና የተለያዩ ስፖርቶች የመጫወቻ ዘዴዎችን ያብራሩለት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ስዕሎቹን እንዲቀባ ያድርጉ።
- ከዚያም **መሞከር የምትፈልገው የበጋ ወቅት ስፖርት ምንድን ነው? ለምን?** ብለው ይጠይቁት።
- ከእያንዳንዱ እግርዎ በታች የሰም ወረቀት ወይም ወረቀት በማስቀመጥ እና የሚንሸራተቱ ለማስመሰል በዝግታ በመንቀሳቀስ አንዳንድ የስፖርት አይነቶችን አስመስለው ሊተውኑ ይችላሉ።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ሰኞ

እውቀት፥ ርዕስ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የትኛውም መጽሀፍ

- ለልጅዎ የመጽሀፍ ሽፋን ያሳዩት። ከዚያም **ርዕስ የመጽሀፉ ስም ነው። ርዕስ በመጽሀፉ የፊት ሽፋን ላይ ይጻፋል** ብለው ይንገሩት። የመጽሀፉን ርዕስ ጠቁመው በማሳየት ያንብቡለት። ከዚያም ርዕሱን ደግሞ እንዲነግርዎት ያድርጉ።
- አንድ ላይ ሆናችሁ መጽሀፉን አንብቡ። ከዚያም **ያነበብነው መጽሀፍ ርዕሱ ምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት።
- ይህን ተግባር ልጅዎን ለመጽሀፉ ሊሰራ የሚችል ሌላ ርዕስ እንዲያስብ በመጠየቅ ማስፋት ይችላሉ።

ያንብቡ፥ *ወደ ውጭ ወጥቶ መጫወት/**Go Outside and Play***

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ [*ወደ ውጭ ወጥቶ መጫወት/Go Outside and Play*]

- ምንባቡን አንድ ላይ ሆናችሁ አንብቡ።
- ከዚያም ሁለታችሁም ወደ ውጭ ወጥታችሁ መጫወት ስለምትወዱባቸው ዘዴዎች ተነጋገሩ። ልጅዎን በኋላ ላይ ሁለታችሁም ውጭ ወጥታችሁ የምታደርጉትን ነገር እንዲጠቁም ያበረታቱት።

በተጨማሪም [ወደ ውጭ ወጥቶ መጫወት/Go Outside and Play] በቅድሚያ የተቀዳ ምንባብን ከዩቲዩብ *ሁሌንም ህጻናት ዝግጁ ማድረግ ቻነል/* [*Every Child Ready* YouTube channel] ላይ ማግኘት ትችላላችሁ።

ወደ ውጭ ወጥቶ መጫወት



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

የበጋ ወቅት ስፖርቶች

ስኬቲንግ



ስሌዲንግ



ስኪዪንግ

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ማክሰኞ

STEM: የውሀ ዛይሎፎን

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከ3-5 ብርጭቆዎች ወይም ጣሳዎች፣ የብረት ወይም የእንጨት ማንኪያ፣ ውሀ፣ *በአማራጭነት- የምግብ ማቅለሚያ*

- ብርጭቆዎቹን በተለያየ መጠን በውሀ ይሙሏቸው። በአማራጭነት የምግብ ማቅለሚያ ይጨመሩ።
- ከልጅዎ ጋር ሆነው ስለ ድምጸና የምት መጠን ተመራመሩ። **ምት የደመጹ ከፍታ ወይም ዝቅታ መጠን ነው** ብለው ይንገሩት። ስለ ከፍተኛ እና ዝቅተኛ የድምጽ ምትለመግለጽ ድምጽዎን ይጠቀሙ።
- **የትኛው ብርጭቆ ከፍተኛ የድምጽ ምት ይፈጥራል ብለህ ታስባለህ? የትኛው ብርጭቆ ዝቅተኛ የድምጽ ምት ይፈጥራል ብለህ ታስባለህ?** ብለው ይጠይቁት። በዝግታ ብርጭቆዎቹን በማንኪያ መታ መታ ያድርጓቸው። ከፍተኛና ዝቅተኛ የደምጽ ምቶችን ለዩ። ሙሉ ውሀ የሚይዘው ብርጭቆ ዝቅተኛ የድምጽ ምት የሚሰጥ ሲሆን ጎዶሎው ብርጭቆ ከፍተኛ የድምጽ ምት ይሰጣል።
- ይህን ተግባር ለማስፋት አንድ ላይ ሆናችሁ ብርጭቆዎቹን እንደ መሳሪያ በመጠቀም ሙዚቃዎች ልትጫወቱ ትችላላችሁ።

በግል መማር፥ የስፖርት ልብስ/ጀርሲ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለሮች፣ [የስፖርት ልብስ/ጀርሲ]

- ለልጅዎ **ጀርሲዎች ስፖርቶችን በምነጫወትበት ወቅት የምንለብሳቸው ማሊያዎች ናቸው። ማሊያዎቹ የቡድኑ ስም፣ የተጫዋቹ ስምና ቁጥር ይጻፍባቸዋል** ብለው ይንገሩት። አንድ ላይ ሆናችሁ ማሊያዎችን ከስልክዎ ወይም ታብሌትዎ ላይ ተመልከቱ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ የራሱን ማሊያ ዲዛይን እንዲያዘጋጅና እንዲቀባ ያድርጉ።
- ከዚያም **ስለ ማሊያህ ልትነግረኝ ትችላለህ? የቡድንህ ስም ማን ነው? አንተ ስንት ቁጥር ነህ?** ብለው ይጠይቁት።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ማክሰኞ

እውቀት፥ ደራሲና ሰዐሊ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የትኛውም መጽሀፍ

- ለልጅዎ የመጽሀፉን ሽፋን ያሳዩት። ከዚያም **ደራሲ ቃላቱን የሚጽፈው ሰው ነው። ደራሲው የመጽሀፉን ታሪክ ይጽፋል** ብለው ይንገሩት። የደራሲውን ስም ጠቁመው ያሳዩትና ያንብቡለት። ከዚያም ደግሞ እንዲናገር ያድርጉ።
- **ሰዐሊ በመጻህፍት ውስጥ የሚገኙ ስዕሎችን የሚስለው ሰው ነው** ብለው ይንገሩት። የሰዐሊውን ስም ጠቁመው ያሳዩትና ያንብቡለት። ከዚያም ደግሞ እንዲናገር ያድርጉ።
- መጽሀፉን አንድ ላይ ሆናችሁ አንብቡ። ከዚያም **ያነበብነው መጽሀፍ ደራሲው ማን ነው?** ብለው ይጠይቁት። ስዕሎችን ጠቁመው ያሳዩት። ከዚያም **የወደድከው ስዕል ወይም ምስል የትኛው ነው? ለምን?** ብለው ይጠይቁት።
- ይህን ተግባር ለማስፋት ልጅዎን ደራሲ ቢሆን ለመጻፍ ስለሚፈልገው ታሪክ እንዲገልጽልዎ ሊጠይቁት ይችላሉ። ልጅዎ በተጨማሪም የመጽሀፉን ርዕስ ሊመርጥ ይችላል። ታሪኩን በሌላ ጊዜ ሊጽፍና ሊስል ይችላል።

የጆርናል ሙከራ፥ ከቤት ውጭ መዝናኛ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለሮች፣ ከቤት ውጭ መዝናኛ

- ከለልጅዎ ጋር ከቤት ውጭ መጫወት ስለሚወድባቸው ዘዴዎች ተነጋገሩ።
- ለልጅዎ እራሱን ችሎ እነዚህን እንዲጽፍና እንዲስል ይፍቀዱለት።
- ከዚያም **ከቤት ውጭ ምን መስራት ትወዳለህ? ይህን መስራት የምትወደው ለምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ _________________

ከቤት ውጭ ምን ምን ነገሮችን መስራት ያስደስታችኋል?

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ረቡዕ

PK3 ክፍል 11 ሳምንት 2 ቀን 8

STEM: ጃኮችን መዝለል

- ከእንቅስቃሴዎች ጋር እስከ 10 መቁጠር ተለማመዱ።
- ከልጅዎ ጋር ሆነው 8 ጃኮችን ለመዝለል ሞክሩ። ስለ ጃክ አዘላለል ያሳዩት። አብራችሁ እጆቻችሁን ወደ ጎን በመዘርጋት ቀጥ ብላችሁ ቁሙ። እግሮቻችሁን ከፍታችሁ እና አጆቻችሁን ከራሳችሁ በላይ እያገናኛችሁ ዝለሉ። ወደ ኋላ ወደነበራችሁበት ቦታ እየዘለላችሁ 1 ብላችሁ ቁጠሩ። እስከ 10 እየቆጠራችሁ መዝለላችሁን ቀጥሉ።
- ልጅዎ ዝግጁ ከሆነ ከ10 በላይ ቁጥሮችን ቁጠሩ።

በግል መማር፥ የበጋ ወቅት ስፖርቶች

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለሮች፣ ወረቀት፣ [የበጋ ወቅት ስፖርቶች]

- ስዕሎቹን በመጠቀም ከልጅዎ ጋር እንደ በውሀ ላይ መንሳፈፍ፣ የእጅ ኳስ፣ ቤዝቦል ወይም መንሸራተት ስለመሳሰሉ የበጋ ወቅት ስፖርቶች ተነጋገሩ። የሚያስፈልገው መሳሪያና ስፖርቱ እንዴት እንደሚሰራ በተመለከተ ያብራሩ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ስዕሎቹን እንዲቀባ ያድርጉ።
- ከዚያም **መሞከር የምትፈልገው የበጋ ወቅት የስፖርት አይነት ምንድን ነው? ለምን?** ብለው ይጠይቁት።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ረቡዕ

PK3 ክፍል 11 ሳምንት 2 ቀን 8

እውቀት፥ መስመሮች መሳል



አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለሮች፣ ወረቀት፣ [መስመሮች 2]

- ልጅዎን እራሱን ችሎ በተሰጠው ገጽ ላይ መስመሮቹን ፈልጎ እንዲከተል ያድርጉ።
- ልጅዎ በተጨማሪም ፈልጎ ከመከተል ይልቅ በቁራጭ ባዶ ወረቀተ ላይ የቁመት፣ አገደመት እና ከርቭ መስመሮችን መሳል ሊለማመድ ይችላል።

ያንብቡ፥ *ወደ ውጭ ወጥቶ መጫወት/Go Outside and Play*

ወደ ውጭ ወጥቶ መጫወት



አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ *[ወደ ውጭ ወጥቶ መጫወት/Go Outside and Play]*, **የመጫወቻ ሊይ ወይም** [በመጫወቻ ሊጥ የተዘጋጀ]

- ምንባቡን ከልጅዎ ጋር ሆነው ያንብቡ።
- ከዚያም ልጅዎን ከታሪኩ ውስጥ የሚወዳቸውን ነገሮች እንዲመርጥ ይጠይቁት፤ ለምሳሌ፡ አበቦች፣ የንብ ቀፎ ወይም ጥንቸል፣ እና ከዚያም እነዚህን የመጫወቻ ሊጥ በመጠቀም እንዲሰራቸው ይጠይቁት።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ረቡዕ

PK3 **ክፍል** 11 **ሳምንት** 2 **ቀን** 8

እስኪ እንንቀሳቀስ፥ ስሜትን በቀላሉ መረዳት



አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ [የስሜት ፖስተር](); መቀስ

- የተለያዩ ካርዶችን ለማዘጋጀት ስሜቶችን ቆርጠው ያውጡ።
- ስሜትን በቀላሉ የመረዳት ጌም ተጫወቱ። ስሜት ይምረጡ። በካርዱ ላይ ያለውን ስሜት አስመስለው ለመተወን የሰውነት ቋንቋና የፊት ገለጻዎች ይጠቀሙ። ልጅዎን እርስዎ የሚያሳዩትን ስሜት እንዲገምት ያድርጉ። ከዚያም **ይህ** __(ስሜት)__ **እንደተሰማኝ በምን አወቅክ?** ብለው ይጠይቁት።
- ሚናችሁን ተቀያየሩ። ልጅዎ እርስዎ የሚገምቱትን ስሜት እንዲያሳይ ያድርጉ።

ካርዶቹን በሳምንት 3 እና 4 ለመጠቀም ያስቀምጧቸው።

አንድ ላይ ሆኖ መማር፥ ስፖርታችን

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ በምትመርጠው ተግባር ላይ ተመስርቶ

- ከልጅዎ ጋር ሆነው ስለሚወዳቸው ስለተለያዩ የስፖርት አይነቶች እና የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎች በተመለከተ ተነጋገሩ። ከዚያም **ስፖርት ወይም እንቅስቃሴ መስራት ብትችል ምን መስራት ትፈልጋለህ?** ብለው ይጠይቁት።
- ልጅዎን ስለ ተግባሩ እንዲያስብ ያድርጉት እና ከዚያም ተግባሩን በጋራ ስሩና እንዴት እንደሰራችሁ ተነጋገሩ።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

የበጋ ወቅት ስፖርቶች

ቮሊ ቦል

ሰርፊንግ



ስኬትቦርዲንግ

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።



ደስተኛ



ሃዘን

ንዴት

የተረበሸ

የተረጋጋ

ኩራት

ሃዘን

እንቅልፍ መጫጫን

በጣም መደሰት

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ሃሙስ

STEM: የድምጽ ሞገዶች

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ 2 የፕላስቲክ ኩባያዎች፣ ከ10-20 ጫማ ክሮች፣ መቀስ

- የእያንዳንዱ ኩባያ ስር ላይ ትንሽ ቀዳዳ ለመብሳት መቀስ ይጠቀሙ። ክሩን በእያንዳንዱ ቀዳዳ ውስጥ ያሳልፉና ቋጠሮ ይስሩ።
- **ድምጽ በአየር ሞገድ አማካኝነት ያልፋል። በእነዚህ ኩባያዎች ውስጥ እርስ በርስ ማውራት የምንችል ሲሆን የድምጽ ሞገዶች በክሮቹ ውስጥ ያልፋሉ** ብለው ይንገሩት።
- ሁለታችሁም ኩባያ ያዙ። በዝግታ እርስ በርሳቹ ክሩ እስከሚጠብቅ ድረስ ተላለፉ። እርስዎ በኩባያው ውስጥ በሚናገሩበት ወቅት ልጅዎን ኩባያውን ወደ ጆሮው አስጠግቶ እንዲይዝ ያድርጉ። ሚናችሁን ተቀያየሩ። ልጅዎ ሲናገር እርስዎ ያዳምጡ።
- ከዚያም **ድምጽ ከእኔ አፍ ወደ አንተ ጆሮ ይተላለፋል!** ብለው ይንገሩት።

በግል መማር፥ የምወደው ስፖርት

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለሮች፣ ወረቀት፣ [ስፖርቶች ቀለም መቀባት]



- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስለተለያዩ ስፖርቶች ተነጋገሩ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ስዕሎቹን ቀለም እንዲቀባና ስለሚወደው የስፖርት አይነት እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ቀጥለውም **የምትወደው የስፖርት አይነት ምንድን ነው? ይህን** __(ስፖርት)__ **የምትወደው ለምንድን ነው? ይህን** __(ስፖርት)__ **የምትጫወተው እንዴት ነው?** ብለው ይጠይቁት።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ሃሙስ

እውቀት፥ ቃላት እና ስዕሎች

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የትኛውም መጽሀፍ

- ከማንበብዎ በፊት ለለጅዎ ቃላቱን ጠቁመው ያሳዩት። ከዚያም **ቃላቱ በታሪኩ ውስጥ ምን እንደተከናወነ ይነግሩናል** ብለው ይንገሩት። ስዕል ጠቁመው ያሳዩት። **ስዕሉ ይህ ምን እንደሚመስል ያሳየናል** ይበሉት።
- አንድ ላይ ሆናችሁ መጽሀፉን አንብቡ። በምታነቡበት ወቅት እያንዳንዱን ቃል በማመልከት ለህትመቱ ትኩረት ስጡ።
- ካነበባችሁ በኋላ ልጅዎን በመጀመሪያ ቃላቱን ቀጥሎም ስዕሎቹን ጠቁሞ እንዲያሳይዎት ይጠይቁት።
- ይህን ተግባር ለቁሶቹ ስም በመስጠት እና ልጅዎን የቁሱን ስዕል እንዲስል በመጠየቅ ከዚያም ሚናዎቻችሁን በመቀያየር ማስፋት ተችላላችሁ። ወይም ተራ በመቀያየር ቁሶችን በመሳል እና ቁሱ ምን እንደሆነ በመጠያየቅ ስም የመገመት ጌም ልትጫወቱ ትችላላችሁ።

የጆርናል ሙከራ፥ የስፖርት ሙከራ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የስፖርት ሙከራ፣ ከለሮች

- ከልጅዎ ጋር ሆነው ስለተለያዩ ስፖርቶችና መሞከር ስለሚፈልገው የስፖርት አይነት ተነጋገሩ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ስለ ስፖርት አይነቱ እንዲጽፍና እንዲስል ያድርጉ።
- ከዚያም **ይህን ስፖርት መሞከር የምትፈልገው ለምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት። ከተቻለ ይህን ስፖርት በጋራ ሞክሩ።

ስም፥ ________________

ከቤት ውጭ ምን ምን ነገሮችን መስራት ያስደስታችኋል?

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።



የቅርጫት ኳስ

የቤዝቦል ኳስ

የእግር ኳስ

የቴኒስ ኳስ

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ ________________

መሞከር የምትፈልጉት ስፖርት የትኛውን ነው፣ ለምን?

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

አርብ

PK3 ክፍል 11 ሳምንት 2 ቀን 10

STEM: ጉልበትን ከፍ ማድረግ

- ከልጅዎ ጋር ከእንቅስቃሴዎች ጋር እስከ 10 መቁጠር ተለማመዱ።
- አንድ ላይ ሆናችሁ እስከ 10 ጊዜ ጉልበት ከፍ ማድረግ ሞክሩ። ጉልበት ከፍ ማድረግ ያሳዩት። የቀኝ ጉልበትዎን እስከ ደረትዎ ድረስ ወደ ላይ ከፍ ያድርጉ። የግራ ጉልበትዎን በመቀየር እስከ ደረትዎ ድረስ ወደ ላይ ከፍ ያድርጉ። እግራችሁን እያቀያየራችሁና ጉልበታችሁን ከፍ በምታደርጉበት በእያንዳንዱ ጊዜ እየቆጠራችሁ እንቅስቃሴውን መስራት ቀጥሉ።
- ልጅዎ ዝግጁ ከሆነ ከ10 በላይ ቀጥሮችን ቁጠሩ።

በግል መማር፡ የፖፕሲክል አርት

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለሮች፣ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ማጣበቂያ፣ መቀስ፣ [የፖፕሲኮል መቀቢያ]



- ልጅዎን እራሱን ችሎ ፖፕሲክሉን ቀለም እንዲቀባና ቆርጦ እንዲያወጣ ያድርጉ።
- ልጅዎን ፖፕሲክሉን እርሳስ ላይ እንዲያጣብቅ ይርዱት።
- ***ፖፕሲክልህ ምን አይነት ስሜት አለው? ይቀዘቅዛል ወይስ ይሞቃል?*** ብለው ይጠይቁት።
- ይህን ተግባር ለማስፋፋት እርስዎና ልጅዎ ጭማቂ በማቀዝቀዝ ወይም ፍራፍሬዎችን በፖፕሲክል ማጣበቂያዎች፣ የበረዶ ኩባያዎች ወይም በከፊል የቀዘቀዘ ከሆነ የጥርስ መፋቂያ ወይም የፖፕሲክል ቀጭን ስንጥር በተጨመረባቸው ትናንሽ ኩባያዎች ውስጥ በመቀላቀል ቀላል ፖፕሲክሎችን ልትሰሩ ትችላላችሁ።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

አርብ

PK3 ክፍል 11 ሳምንት 2 ቀን 10

እውቀት፥ ማንበብና መሳል

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የትኛውም መጽሀፍ፣ ወረቀት፣ ከለሮች

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ልጅዎ የሚመርጠውን መጽሀፍ አንብቡ።
- ካነበባችሁ በኋላ ልጅዎን ከታሪኩ ውስጥ ስለወደደው ኩነት እንዲስል ያድርጉ።
- **በስዕልህ ላይ ምን እየተደረገ ነው?** ብለው ይጠይቁት። የልጅዎን ምላሽ ይጻፉና መልሰው ያንብቧቸው። ይህ ለልጅዎ ቃላቱ ሊጻፉ እንደሚችሉና ትርጉም እንዳላቸው እንዲያውቅ ያደርገዋል።

ያንብቡ፥ ወደ ውጭ ወጥቶ መጫወት/Go Outside and Play

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ *ወደ ውጭ ወጥቶ መጫወት/Go Outside and Play*

- ምንባቡን ከልጅዎ ጋር ሆነው ያንብቡ።
- ከዚያም እርስዎና ልጅዎ በሰውነታችሁ ቅርጽ ልትሰሩ ትችላላችሁ፤ ለምሳሌ፡ ከራሳችሁ በላይ በእጆቻችሁ ክብ/ሞላላ/ሶስት ማዕዘን ቅርጽ መስራት ወይም በጣቶቻችሁ ሶስት ማዕዘን ቅርጽ መስራት። የሁለታችሁንም ሰውነት አንድ ቅርጽ ለመስራት አንድ ላይ መጠቀምም ትችላላችሁ!

ወደ ውጭ ወጥቶ መጫወት



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ሳምንት 3

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

የPK3 ክፍል 11 ሳምንት 3 ጠቅላላ ምልከታ

የበጋ ወቅት እራስን መንከባከብ

በዚህ ሳምንት ልጅዎ፥

በዚህ ሳምንት ልጅዎ እራስን ስለመንከባከብ፣ የተለያዩ የመረጋጊያ ቴክኒኮችን ስለ መለማመድ ትኩረት ያደርጋል እንዲሁም ጤናማና ደህንነት ጠብቆ ስለመቆየጥ ይማራል። ልጅዎ በተጨማሪም መቁጠርና የቃላት ድምጾችን መቀላቀል እና እስከ 10 መቁጠር ይለማመዳል።

ቁልፍ ቃላት

መረጋጋት

ሰውነትን ማፍታታት፣ ፀጥታ፣ አለመናደድ፣ ስሜታዊ አለመሆን ወይም አለመበሳጨት ነው

ጤናማነት

አለመታመም ወይም የሰውነታችን ጥሩ መሆን ነው

የደህንነት መጠበቅ

አለመጎዳት ነው

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

በዚህ ሳምንት እራስን ስለመንከባከቢያና ጤናና ደህንነትን ጠብቆ ስለመቆያ ዘዴዎች ትማራላችሁ። መረሀግብሩን ከመጀመርዎ በፊት ስለ አንዱ እእስዎን መንከባከቢያ ዘዴ ይጻፉ እንዲሁም ይሳሉ።

ያስቡበት!

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ሰኞ

STEM: የቁጥር ተያያዥነቶች

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ማጣበቂያ፣ መቀስ



- ወረቀት በሸንተረር ይቁረጡ። የወረቀት ሸንተረርና ክር በመጠቀም አንድ ሉፕ ይስሩ። ለልጅዎ እንዴት ሉፕ እንደሚሰራ ያሳዩት እና ተጨማሪ ሉፖች አበራችሁ ሰሩ።
- እያንዳንዱን ሉፕ ከመደመራችሁ በፊት በሰንሰለቱ ውስጥ ምን ያክል ሉፖች እንዳሉ ቁጠሩ። ይህ ለልጅዎ የመጀመሪያ የመደመር ስትራቴጂዎችን ያስተምረዋል።
- ሙከራውን የሰንሰለታችሁ ሉፖች 10 እስከሚሞሉ ድረስ ደግማችሁ ስሩ። ልጅዎ ለመቁጠር እንዲረዳው ሉፖችን በመጠቀሙ ሊቀጥል ይችላል። ልጅዎን ሰንሰለቱን ሊያሳምርና የሚሰቅልበትን ቦታ ሊመርጥ ይችላል።

በግል መማር፥ ጤናማ ሆኖ መቀጠል

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለሮች

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ጤናማ ሆኖ መቆየት ስለሚቻልባቸው ዘዴዎች ተነጋገሩ፤ ለምሳሌ፡ ውሀ መጠጣት፣ እረፍት ማድረግ እና እንቅስቃሴ መስራት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ጤንነቱን ስለሚጠብቅባቸው ዘዴዎች እንዲጽፍና እንዲስል ያድርጉ።
- ከዚያም **ጤንነትህን የምትጠብቀው እንዴት ነው? የምትወደው የእንቅስቃሴ አይነት ምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ሰኞ

እውቀት፥ የቃላት ድምጾችን መደርደር

- ልጅዎን **የቃላት ድምጾች የድምጽ ምት ናቸው። እስኪ ball የሚለውን ቃል ድምጽ እንደረድር** ይበሉት። አንድ ቃል ይጥሩና ድምጾቹን አንድ ጊዜ ይደርድሩ። **ball የሚለው ቃል አንድ ድምጽ አለው** ብለው ይንገሩት።
- በሌሎች እንደ base-ball፣ sports፣ bas-ket-ball፣ gym-nas-tics በመሳሰሉ ባለ 1-3 ድምጽ ያላቸው ቃላት ድምጾችን ይደርድሩ።

ያንብቡ፥ *የተረጋጋ ሰውነት መጽሀፍ/The Calm Body Book*

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ *የተረጋጋ ሰውነት መጽሀፍ/The Calm Body Book*

- ለልጅዎ **የሰውነታችንን ጤናና ብቁነት የመጠበቅ እጅግ አስፈላጊው ክፍል ሰውነታችንን እና አእምሯችንን ለማረጋጋት ይረዳናል** ብለው ይንገሩት።
- ከልጅዎ ጋር የመጽሀፉን ገጽ. 2-11 አንብቡና እነዚህን የትንፋሽ አወሳሰዶች በመሞከር በጋራ ተለማመዱ።
- ልጅዎን የሚወደውን የትንፋሽ አወሳሰድ እንዲመርጥ ያበረታቱትና ይህን ከ1-2 ጊዜያት አንድ ላይ ሞክሩ።
- እነዚህን ትንፋሽ አወሳሰዶች ቀኑን በሙሉ መሞከር ልጅዎን እንደ ንዴት አይነት ስሜቶች በሚፈጠሩበት ወቅት እራሱን ለማረጋጋት ወይም የተሻለ ስሜት ለማግኘት ለመጠቀም እንዲረዳው ከትንፋሽ አወሳሰዶቹ ጋር ለመላመድ ይረዳዋል።

በተጨማሪም የተረጋጋ ሰውነት መጽሀፍ/The Calm Body Book በቅድሚያ የተቀዳ ምንባብን ከዩቲዩብ *ሁሉንም ህጻናት ዝግጁ ማድረግ ቻነል/ Every Child Ready* YouTube channel ላይ ማግኘት ትችላላችሁ።

የተረጋጋ ሰውነት መጽሀፍ



ደራሲ፥ ፎኒክስ ሊን ሚንክሌይ ፈርሚን
ሰዓሊ፥ ራቼል አኒ ብሌር

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ማክሰኞ

PK3 ክፍል 11 ሳምንት 3 ቀን 12

STEM: የሰውነት አካል ስዕሎች

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለሮች፣ ***በአማራጭነት - የመንገድ ጠርዝ መቀቢያ ጠመኔ***

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው የሰው አካል ንድፍ ሳሉ። በተጨማሪም ወደ ውጭ መውጣትና ልጅዎን በጠመኔ መሳል ወይም ልጅዎ እርስዎን በጠመኔ ሊስልዎት ይችላል።
- አይኖችዎን ጠቁመው ያሳዩ እና **ይህ የትኛው የሰውነት ክፍሌ ነው?** ብለው ይጠይቁት። ልጅዎን በሰወነት ንድፉ ላይ አይኖችን እንዲስልና መልክት እንዲያደርግ ይርዱት። ሙከራውን በአፍንጫ፣ ጆሮዎች፣ አፍ፣ የእጅና የእግር ጣቶች ደግማችሁ ስሩ። ሌሎች የአካል ክፍሎችንመ ለትጨምሩ ትችላላችሁ።
- ልጅዎን የሰውነት አካሉን በማስዋብ እንዲዝናና ያድርጉት!

በግል መማር፥ ካርዶች ማሰር

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ካርቶን፣ መቀስ፣ ክር፣ ሲባጎ ወይም የጫማ ማሰሪያዎች

- ካርቶን እንደ ሶስት ማዕዘን ወይም ልጅዎ የሚወደው እንስሳ በመሳሰሉ ቅርጾች ቆርጠው ያውጡ። በካርቶኑ ቅርጽ ዙሪያ ትናንሽ ቀዳዳዎች ለመብሳት መቀስ ይጠቀሙ፡ ክር (ወይም ሲባጎ ወይም የጫማ ማሰሪያ) ቆርጠው ያውጡና መጨረሻቸው ላይ ይቋጥሯቸው።
- ልጅዎን በቀዳዳዎቹ ላይ ክር እንዲያስር ያድርጉ።
- ካርዶችን ማሰር ለልጆች ትናንሽ እንቅስቃሴዎችን በእጃቸው፣ ጣቶቻቸውና አውራ ጣታቸው መቆጣጠር እንዲለማመዱ ያስችላቸዋል። ይህ ለቀላል እንቅስቃሴ እድገት ጥሩ ነው!

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ማክሰኞ

እውቀት፥ የቃላት ድምጾችን መቁጠር

- ለልጅዎ **የቃላት ድምጾች የቃላት ምቶች ናቸው። እስኪ run የሚለውን ቃል እናያይዝና ድምጾቹን እንቁጠር** ብለው ይንገሩት። ቃሉን ይጥሩና ያያይዙት። ከዚያም ልጅዎን **run በሚለው ቃል ውስጥ ምን ያክል ድምጾች አሉ?** ብለው ይጠይቁት።
- ሌሎች እንደ goal፣ soc-cer፣ ex-er-cise የመሳሰሉ ከ1-3 ድምጾች ያላቸው ቃላትን በማገናኘት ድምጻቸውን ቁጠሩ።

የጆርናል ሙከራ፥ የመኝታ ሰዐት መደበኛ ተግባሬ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለሮች፣ የመኝታ ሰዐቴ

- ከልጅዎ ጋር ለመኝታ ስትዘጋጁ ምን እንደምታደርጉ ነጋገሩ፤ ለምሳሌ፡ የሌሊት ልብስ መልበስ፣ ጥርስ መፋቅ እና ታሪክ ማንበብ።
- ልጅዎን ራሱን ችሎ ስለ መኝታ ሰዐት መደበኛ ተግባሩ እንዲጽፍና እንዲስል ያድርጉ።
- ከዚያም **ለመኝታ ሰዐትህ ስትዘጋጅ ምን ታደርጋለህ? የምትወደው የመኝታ ሰዐት ተግባር ምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ _________________

ስለመኝታ ሰዐት መደበኛ ተግባራችሁ ጻፉ እንዲሁም ስዕል ስሩ።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ረቡዕ

STEM: ከ1 እስከ 10 መቁጠር

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ እንደ ቁልፎች ወይም ጠጠሮች የመሳሰሉ ትናንሽ ቁሳቁሶች፣ ***በአማራጭነት*** **-** ***10 ፍሬም***



- በአንድ ሳጥን አንድ ቁስ በማድረግ 7 ቁሶችን በ10 ፍሬም ላይ ያስቀምጡ። በሚቆጥሩበት ወቅት እያንዳንዱን ቁስ ጠቁመው ያሳዩ። ከዚያም ልጅዎን ቁሶቹን ጠቁሞ እንዲያሳይና እንዲቆጥር ያድርጉ።
- የተለየ ብዛት ያላቸው ቁሶችን ከ1-10 ቁጠሩ።

በግል መማር፥ የቡድን ባንዲራ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለሮች፣ ባንዲራ



- የባንዲራ ስዕል ፕሪንት ያድርጉ ወይም ይሳሉ።
- ለልጅዎ **ባባዲራዎች የምትወደውን ስፖርት ወይም ቡድን የምታሳይባቸው ሰንደቅ አላማዎች ናቸው** ብለው ይንገሩት። አንድ ላይ ሆናችሁ የባንዲራ ስዕሎችን ከስልክዎ ወይም ታብሌትዎ ላይ ተመልከቱ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ የሚመርጠውን ባንዲራ እንዲስልና ቀለም እንዲቀባ ያድርጉ።
- ከዚያም **የሳልከው ምንድን ነው? ይህን ባንዲራህ እንዲሆን ለምን መረጥከው?** ብለው ይጠይቁት።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

እውቀት፥ የቃላት ድምጾችን መቀላቀል

- ለልጅዎ **እስኪ የቃላት ድምጾችን እንቀላቅል! መቀላቀል ማለት አንድ ላይ ማድረግ ነው** ብለው ይንገሩት።
- **እኔ ሁለት የቃላት ድምጾችን እነግርሀለሁ። አንተ ደግሞ ድምጾቹን አንድ ላይ በመቀላቀል ቃሉን ትነግረኛለህ። Soc** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **cer. Soc-cer** ብለው ይንገሩትና **ቃሉ ምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት።
- እንደ bowl-ing፣ ten-nis፣ hock-ey የመሳሰሉ ሌሎች ባለ 2 ድምጽ ቃላትን በመጠቀም ደግማችሁ ስሩ።

ያንብቡ፥ የተረጋጋ ሰውነት መጽሀፍ/The Calm Body Book

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ *የተረጋጋ ሰውነት መጽሀፍ/The Calm Body Book*

- ከልጅዎ ጋር እንደ ብስጭት ወይም ሀዘን የመሳሰሉ ጠንካራ ስሜቶች ሲፈጠሩበት ምን እንደሚሰማው በተመለከተ ተነጋገሩ። ጥሩ ስሜት ሊፈጥሩለት የሚችሉ የተለያዩ ነገሮች እንዳሉ ያብራሩለት፤ ለምሳሌ፡ የተለያዩ የትንፋሽ መውሰድና የመተንፈስ እንቅስቃሴዎች። ለልጅዎ እነዚህ ስሜቶች ቢያጋጥሙ ምንም ማለት እንዳልሆነ ያስታውሱት!
- ከልጅዎ ጋር የመጽሀፉን ገጽ. 2-3 እና ገጽ 12-19 አንብቡና እነዚህን የትንፋሽ አወሳሰዶች በመሞከር በጋራ ተለማመዱ።
- ልጅዎን የሚወደውን የትንፋሽ አወሳሰድ እንዲመርጥ ያበረታቱትና ይህን ከ1-2 ጊዜያት አንድ ላይ ሞክሩ። **ይህን ትንፋሽ አወሳሰድ ከሰራህ በኋላ ሰውነትህ ምን አይነት ስሜት ተሰማው?** ብለው ይጠይቁት።

እነዚህን ትንፋሽ አወሳሰዶች ቀኑን በሙሉ መሞከር ልጅዎን እንደ ብስጭት አይነት ስሜቶች በሚፈጠሩበት ወቅት እራሱን ለማረጋጋት ወይም የተሻለ ስሜት ለማግኘት ለመጠቀም እንዲረዳው ከትንፋሽ አወሳሰዶቹ ጋር ለመላመድ ይረዳዋል።

የተረጋጋ ሰውነት መጽሀፍ



ደራሲ፥ ፎኒክስ ሊን ሚንክሌይ ፈርሚን
ሰዓሊ፥ ራቼል አኒ ብሌር

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ረቡዕ

PK3 ክፍል 11 ሳምንት 3 ቀን 13

እስኪ እንንቀሳቀስ፥ ሲሞን ይላል

- ለልጅዎ **የቡድን ተጫዋች ለመሆን በሌሎች የሚሰጡህን መመሪያዎች መከተል መቻል እና ተራህን ጠብቀህ መመሪያዎች መስጠት ይኖርብሀል። እስኪ ለመለማመድ ሲሞን ይላል ጨዋታ እንጫወት** ብለው ይንገሩት።
- በዚህ ጌም ውስጥ ልጅዎ ሲሞን የሚላቸውን ነገሮች ብቻ ማድረግ ይኖርበታል። **ሲሞን የቅርጫት ኳስ አንጥር ይላል** ይበሉት። ልጅዎ ኳሱን የሚያነጥር አስመስሎ መተወን አለበት። ከዚያም **የሌሊት ወፍ አወዛውዝ** ይበሉት። ልጅዎ ልክ እንደ የሌሊት ወፍ ክንፉን የሚያወዛውዝ አስመስሎ ከተወነ **ኦ፤ እኔ ይህን ሲሞን ይላል አላልኩም** ይበሉት።
- ጌሙን እንደ የእግር ኳስ መለጋት ወይም የቴኒስ ራኬት ማወናጨፍ የመሳሰሉ የስፖርት እንቅስቃሴዎችን በመጠቀም ብዙ ጊዜ ደግማችሁ ስሩ። ጌሙን የመምራት ተራችሁን ተቀያየሩ።

አንድ ላይ ሆኖ መማር፥ ተራ ስሜቶች

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከቀን 8 የተወሰዱ [**የስሜት ፖስተር**]

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው የተራ ስሜቶች ጨዋታ ይጫወቱ። እንስሳ ምረጡና ከፖስተር ላይ ስሜት ምረጡ። ምርጫዎን አስመስለው ይጫወቱና ልጅዎን ምንን አስመስለው እየተጫወቱ እንደሆነ እንዲገምት ያድርጉ።
- ደስተኛ አንበሳ ለመምሰል ይሞክሩ። በሚያጓሩበት ወቅት ፈገግ ይበሉ።
- ጨዋታውን የተለያዩ ስሜቶችና እንስሳትን ተጠቅማችሁ ደግማችሁ ስሩ።
- ሚናችሁን ተቀያየሩ።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።



ሃሙስ

PK3 ክፍል 11 ሳምንት 3 ቀን 14

STEM: ኦብሌክ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የእቃ መያዣ፣ የማሽላ ስታርች፣ ውሀ፣ ማንኪያ፣ *በአማራጭነት - የምግብ ማቅለሚያ*

- ለልጅዎ **እስኪ ስለ ኦብሌክ እንመራመርና እንጫወት። ኦብሌክ ፈሳሽም ጠጣርም የሚመስል ውህድ ነው** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን 2 እጅ የማሽላ ስታርች እና 1 እፍኝ ውሀ ከምግብ ማቅለሚያ ጋር እንዲቀላቅል ይርዱት (ምሳ፡ 2 ኩባያ የማሽላ ስታርች በ1 ኩባያ ውሀ)።
- ልጅዎን አዝናኝ ጨዋታ እንዲጫወተት እና ኦብሌኩ ፈሳሽ ሲመስልና ጠጣር ሲመስል ለማየት በእጆቹ እና በማንኪያ እንዲመረምር ያበረታቱት።

በግል መማር፥ የደህንነት ፖስተሮች

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለሮች

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው እንደ ብስክሌት ወይም የእግረኛ ደህንነት ስለመሳሰሉ የበጋ ወቅት ደህንነቶች በተመለከተ ተነጋገሩ።
- እንደ ቤተሰብ ለደህንነት የሚጠበቁ ሁኔታዎች ዝርዝር አዘጋጁ፤ ለምሳሌ፡ መንገድ በማቋረጥ ወቅት የአዋቂ ሰው እጅ ይዞ መሻገር ወይም ብስክሌት በማሽከርከር ወቅት ሄልሜት መልበስ።
- ከለጅዎ ጋር ደህንነትን መጠበቅ ለምን እንደሚያስፈልግና ስለተለያዩ የደህንነት መጠበቂያ ዘዴዎች ተነጋገሩ። እንደ እንግዳ ሰዎችን ማናገር፣ የእገረኛ ደህንነት ወይም የጸሀይ መከላከያ መነጽር ማድረግ የመሳሰሉ ህጎችን ተመልከቱ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ስለ ደህንነት ፖስተሮች እንዲጽፍና እንዲስል ያድርጉ።
- ከዚያም **የጻፍከውና የሳልከው ስለ የትኛው የደህንነት ህግ ነው? ለሌሎች ሰዎች ደህንነትን ስለመጠበቅ በተመለከተ ምን ትነግራቸዋለህ?** ብለው ይጠይቁት።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ሃሙስ

እውቀት፥ የቃላት ድምጾችን መቀላቀል

- ለልጅዎ **እስኪ የቃላት ድምጾችን እንቀላቅል! መቀላቀል ማለት አንድ ላይ ማድረግ ነው** ብለው ይንገሩት።
- **እኔ ሁለት የቃላት ድምጾችን እነግርሀለሁ። አንተ ደግሞ ድምጾቹን አንድ ላይ በመቀላቀል ቃሉን ትነግረኛለህ። Fris** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **bee. Fris-bee** ብለው ይንገሩትና **ቃሉ ምንድን ነው? Frisbee!** ይበሉት።
- እንደ hock-ey፣ swim-ming፣ safe-ty የመሳሰሉ ሌሎች ባለ 2 ድምጽ ቃላትን በመጠቀም ደግማችሁ ስሩ። ይህን ተግባር ለማስፋት እንደ sum-mer-time፣ ex-er-cise የመሳሰሉ ባለ 3 ድምጽ ቃላትን ሊያካትቱ ይችላሉ።

የጆርናል ሙከራ፥ እኔ የተረጋጋሁ ነኝ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ እኔ የተረጋጋሁ ነኝ የጆርናል ገጽ፣ ከለሮች

- ከልጅዎ ጋር እንደ ፍርሀት ያለ ጠንካራ ወይም አሉታዊ ስሜት በሚፈጠርበት ወቅት እራሱን ማረጋጋት ወይም የተሻለ ስሜት መፍጠር ስለሚችልባቸው ዘዴዎች ተነጋገሩ። እነዚህ መደነስ፣ ሰዕል መሳል ወይም ትንፋሽ መውሰጃ እንቅስቃሴዎች መስራት ሊሆኑ ይችላሉ።
- ልጅዎን እነዚህን እራሱን ችሎ እንዲጽፍና እንዲስል ያድርጉ።
- ከዚያም **እስኪ እንዴት እራስህን እንደምታረጋጋ ንገረኝ። ይህን ልታሳየኝ ትችላለህ?** ብለው ይጠይቁት።
- ለልጅዎ ጠንካራ ስሜቶች ቢያጋጥሙ ምንም ማለት እንዳልሆነ ያስታውሱት!

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ _________________

እራሳችሁን ለማረጋጋት ስለምታደርጓቸው ነገሮች ጻፉ እንዲሁም ስዕል ሳሉ።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

አረብ

STEM: የስብስቦች ሙከራ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የወረቀት ማስቀመጫ፣ ከለሮች ወይም ሌሎች ትናንሽ ቁሶች

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላ ሆነው ስብስብ ስለመፍጠር ተለማመዱ። ከዚያም **እኔ ቁጥር እጠራለሁ። አንተ ደግሞ የነገሮች ስብስብ ወይም ምድብ የወረቀት ማስቀመጫው ላይ ታስቀምጣለህ** ብለው ይንገሩት።
- አምስት ከለሮች በወረቀት ማስቀመጫው ላይ ያስቀምጡ። ከዚያም **ይህ የሶስት ነገሮች ስብስብ ነው! እስኪ እንቁጠራቸው። 1, 2, 3, 4, 5!** ይበሉት።
- ከዚያም **አሁን ደግሞ የአንተ ተራ ነው! የሰባት ነገሮች ስብስብ ስራ!** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎ እስከ አስር ቁሶች ስብስብ እንዲሰራና ቁሶቹን አንድ ላይ እንዲቆጥራቸው ያድርጉ።
- ይህን ተግባር ለማስፋት ከ0 እስከ 10 የቁጥር ካርዶችን ማዘጋጀትና ልጅዎን ካርድ መርጦ በካርዱ ላይ ካለው ቁጥር ጋር የሚዛመድ ስብስብ እንዲሰራ ማድረግ ይችላሉ።

በግል መማር፥ ዝርግ ሳህኔ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለሮች፣ የምግብ/መጠጥ መደብር በራሪ ሁፎች ወይም መጽሄቶች፣ ዝርግ ሳህኔ, ለህጻናት ተስማሚ መቀስ



- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስለ አምስቱ የምግብ ምድቦች (ፍራፍሬዎች፣ ጥራጥሬዎች፣ ወተት/ስጋ፣ ፕሮቲኖች፣ አትክልት) ተነጋገሩ።
- አንድ ላይ ሆናችሁ የምግብ ስዕሎችን ለማግኘት የምግብ/መጠጥ መደብር በራሪ ሁፎች ወይም መጽሄቶች፣ ወዘተ ተመልከቱ።
- ልጅዎን የምግብ ስዕሎቹን ቆርጦ እንዲያወጣቸው እና በአምስቱ የምግብ ምድቦች እንዲመድባቸው ያድርጉ። ልጅዎ በትክክል ቆርጦ ባያወጣም ምንም ማለት አይደለም። ሙከራው በራሱ ጥሩ ነው!
- ከዚያም **ይህ** __(ምግብ)__**በየትኛው ምድብ ስር ይመደባል? አትክልት ስር ወይስ ፕሮቲን ስር?** ብለው ይጠይቁት።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

አርብ

PK3 **ክፍል** 11 **ሳምንት** 3 **ቀን** 15

እውቀት፥ ገላጭ ቃላት

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ በቤትዎ ወስጥ የሚገኙ ትላልቅና ትናንሽ ቁሶች

- ከልጅዎ ጋር ቁሶቹን አንድ ላይ ፈልጉ። ትልቅ እና ትንሽ ማለት ምን ማለት እነደሆነ ተነጋገሩ።
- አንድ ላይ ሆናችሁ አንድ ቁስ ፈልጉና ትልቅ ወይም ትንሽ ስለመሆኑ ግለጹ። ልጅዎን **ይህ** __(ቁስ)__ __(ትልቅ/ትንሽ)__**ይመስላል-** ብሎ እንዲናገር ያበረታቱት።
- ቁሶችን በተጨማሪም እንደ ቅርጽ፣ ቀለም/ዲዛይን፣ አገልግሎት፣ ወዘተ… የመሳሰሉ ባህሪያትን በመጠቀም መግለጽ ትችላላችሁ።

ያንብቡ፥ የተረጋጋ ሰውነት መጽሀፍ/The Calm Body Book

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ *[የተረጋጋ ሰውነት መጽሀፍ/The Calm Body Book]*

- የመጽሀፉን ገጽ 2-3 እና ገጽ 20-27 ያንብቡ እና ትንፋሽ የሚወሰድባቸው ቦታዎች በጋራ እየሞከራችሁ ተለማመዱ።
- ልጅዎን የሚወደውን ትንፋሽ አወሳሰድ እንዲመርጥ ያበረታቱት እና ይህን ከ1-2 ጊዜያት በጋራ ሞክሩ።

እነዚህን ትንፋሽ አወሳሰዶች ቀኑን በሙሉ መሞከር ልጅዎን እንደ ስጋት ወይም መሰላቸት አይነት ስሜቶች በሚፈጠሩበት ወቅት እራሱን ለማረጋጋት ወይም የተሻለ ስሜት ለማግኘት ለመጠቀም እንዲረዳው ከትንፋሽ አወሳሰዶቹ ጋር ለመላመድ ይረዳዋል።

የተረጋጋ ሰውነት መጽሀፍ



ደራሲ፥ ፎኒክስ ሊን ሚንክሌይ ፈርሚን
ሰዓሊ፥ ራቼል አኒ ብሌር

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ሳምንት 4

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

የPK3 ክፍል 11 ሳምንት 4 ጠቅላላ ምልከታ

እኔ የቡድን ተጫዋች ነኝ

በዚህ ሳምንት ልጅዎ፥

በዚህ ሳምንት ልጅዎ የቡድን ተጫዋች ስለመሆን እና ከአርስዎ ጋር የተወሰነ አዝናኝ ነገር ለማድረግ ቡድን ስለመመስረት ይማራል። ልጅዎ በተጨማሪም ሜዳሊያዎችን ይሰራል፣ ስለ ልቡ ይማራል፣ ከ0-10 ቁጥሮችን ይለያል እንዲሁም ስለ ታሪክ ክፍሎች ይማራል።

ቁልፍ ቃላት

የስፖርት አይነቶች

ሰዎች እርስ በርሳቸው የሚፎካከሩባቸው ተግባሮች

ቡድን

አንድ ላይ ሆነው ከሌላ ቡድን ጋር የሚጋጠሙ ሰዎች ስብስብ ነው

የቡድን አጋር

ከአርስዎ ጋር በተመሳሳይ ቡድን ውስጥ የሚገኝ አባል ነው

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

በዚህ ሳምንት የምግብ አዘጋጅ ባለሙያ ለመሆን የሚችለውን ሁሉ ጥረት ስላደረገው ስለ ማክሲሚሊያን ትማራላችሁ። መርሀግብሩን ከመጀመርዎ በፊት እንዴት የሚቻልዎትን ጥረት እንደሚያደርጉ በተመለከተ ይጻፉ እንዲሁም ይሳሉ።

ያስቡበት!

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ሰኞ

STEM: ቀለሞች

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከ4-8 የተለያየ ቀለም ያላቸው ከለሮቸ ወይም የተቀለሙ ቁሶች

- ከልጅዎ ጋር ሆነው እያንዳንዱን ቀለሞች ተመልከቱ።
- ቀለም ይምረጡ (ለምሳሌ፡ ቀይ)። በቤትዎ ዙሪያ ወይም ከቤት ውጭ በእግር ተንቀሳቀሱ። እንደ ከለር አይነት ቀይ ቀለም ያላቸውን ነገሮች ተመልከቱ።
- አንድ ላይ ሆናችሁ ያገኛችኋቸውን ነገሮች በዝርዝር ጻፉ። ሙከራውን በሌላ ቀለም ደግማችሁ ስሩ።

በግል መማር፥ የስፖርት እቃዎች መስራት

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት ወይም ካርቶን፣ ከለሮች፣ ማጣበቂያ፣ መቀስ ክር ወይም ሲባጎ

- ልጅዎን ራኬትና ብዙ ትላልቅ ክቦች ቆርጦ እንዲያወጣ ይርዱት።
- አንድ ላይ ሆናችሁሁ ስለ የተለያዩ ስፖርቶችና እቃዎች በመነጋገር ስዕሎችን ከስልክዎ ወይም ታብሌትዎ ላይ ተመልከቱ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ የራሱን የሰፖርት እቃዎች ለመስራት እቃዎቹን እንዲጠቀምባቸው ያድርጉ።
- ከዚያም **የሰራኸው የስፖርት እቃ አይነት ምንድን ነው? ይህን** __(የስፖርት እቃ)__**ከዚህ በፊት ተጠቅመህበት ታውቃለህ? የምትጠቀምበት እንዴት ነው?** ብለው ይጠይቁት።
- ልጅዎ ካርቶን የሚጠቀም ከሆነ ኳስ በራኬት ለማንጠር ለመሞከር በተጨማሪም ኳስ፣ የተጠቀለለ ወረቀት ወይም በካልሲ የተሰራ ኳስ ሊጠቀም ይችላል።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ሰኞ

እውቀት፥ ገጸ ባህሪያት

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የትኛውም መጽሀፍ

- ለልጅዎ መጽሀፍ ያንብቡለት። ከዚያም ስለ ታሪኩ ገጸ ባህሪያት ተነጋገሩ።
- **እስኪ ስለ ታሪኩ ንገረኝ። ገጸ ባህሪያቱ እነ ማን ናቸው? ታሪኩ ስለ ማን ነበር?** ብለው ይጠይቁት።

ያንብቡ፥ ማክሲሚሊያን/***Maximilian***፣ ትልቁ የአለማችን እጅግ ድንቅ የምግብ ባለሙያ/***The Greatest Most Extraordinary Chef in the World***

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ *ማክሲሚሊያን/Maximilian፣ ትልቁ የአለማችን እጅግ ድንቅ የምግብ ባለሙያ/The Greatest Most Extraordinary Chef in the World*

- ምንባቡን ከልጅዎ ጋር ሆነው ያንብቡ።
- ከዚያም **የማክሲሚሊያን አባት ብዙ ነገሮች ያስተማሩት ከመሆኑም በተጨማሪ ታዋቂ የምግብ ዝግጅት ባለሙያ እንዲሆን ረድተውታል። ማክሲሚሊያንም በራሱ ብዙ ጥረት አድርጓል። የቡድን አባል በምትሆንበት ወቅት እነተም ተመሳሳዩን ነገር ማድረግ አለብህ። ሙከራ ማድረግና እርስ በርስ መማማር አለብህ** ብለው ይንገሩት። ከልጅዎ ጋር ጥሩ የቡድን አባል መሆን ስለሚቻልባቸው ዘደዴዎች ተነጋገሩ።

በተጨማሪም የ *ማክሲሚሊያን/Maximilian፣ ትልቁ የአለማችን እጅግ ድንቅ የምግብ ባለሙያ/The Greatest Most Extraordinary Chef in the World* በቅድሚያ የተቀዳ ምንባብን ከዩቲዩብ ሁሉንም ህጻናት ዝግጁ ማድረግ ቻነል/ Every Child Ready YouTube channel ላይ ማግኘት ትችላላችሁ።



ማክሲሚሊያን፣ ትልቁ የአለማችን እጅግ ድንቅ የምግብ ባለሙያ

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ማክሰኞ

STEM: ዝግተኛ ልብ፣ ፈጣን ልብ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ [የልብ ቀለም መቀቢያ ቅጽ፣]() **ከለሮች**



- ከልጅዎ ጋር እንቅስቃሴና እራስን ማፍታታት የልብ ምት መጠንን እንደሚቀይር ይነጋገሩ። በማረፊያ አቀማመጥ ልጅዎን የልብ ምቱን ከሁለቱ የእጅ አንጓው መካከል በአንዱ፣ አንገቱ ወይም ደረቱ ላይ የልብ ምቱን እንዲፈልግ ይርዱት። ከዚያም **በምትረጋጋበት ወቅት የልብ ምትህ ዝግ ይላል። አንዳንዴ እንደውም ላትሰማው ትችላለህ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን ለ20 ሰከንዶች ያክል በቦታው ላይ እንዲንቀሳቀስ ያድርጉት። ከዚያም ልጅዎን የልብ ምቱን በድጋሚ እንዲያዳምጥ ይርዱት። **አሁን ምን ይሰማሀል? እንቅስቃሴ በምትሰራበት ወቅት ልብህ የበለጠ ኦክስጂን ስለሚፈልግ የልብ ምትህ ይፈጥናል!** ይበሉት።
- ልጅዎ በተጨማሪም የእርስዎን የልብ ምት ሊፈልግና ሊያዳምጥ ይችላል!
- ከዚያም የልብ ስዕል ቀለም ሊቀባ ይችላል።

በግል መማር፥ ብስክሌት መስራት

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለሮች፣ ክር፣ የአልሙኒየም ፎይል፣ ማጣበቂያ፣ መቀስ



- ልጅዎን ልክ እንደ ጎማ ሁለት ትላልቅ ክቦችን ቆርጦ እንዲያወጣ ይርዱት።
- አንድ ላይ ሆናችሁ የብስክሌት ስዕሎችን ከስልክዎ ላይ ተመልከቱ። የሳይክል ክፍሎችን ተመልከቱ። ልጅዎ ቁሶችን ብስክሌት ለመስራት እንዴት እንደሚጠቀም በተመለከተ ተነጋገሩ፤ ለምሳሌ፡ ፎይል የሳይክል እጀታ ለመስራት።
- ለጅዎን እራሱን ችሎ ቁሶቹን ብስከሌት ለመስራት እንዲጠቀምባቸው ያድርጉ።
- ከዚያም **የብስክሌቱን ኮርቻ ልታሳየኝ ትችላለህ? ጎማዎቹን እንዴት አስገባሀቸው?** ብለው ይጠይቀት።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ማክሰኞ

እውቀት፥ መቼት

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የትኛውም መጽሀፍ

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆናችሁ መጽሀፍ አንብቡ። ሰለ ታሪኩ መቼት ወይም ስለተካሄደበት ቦታ ተነጋገሩ። **የታሪኩ መቼት የት ነው? የታሪኩ ገጸ ባህሪ የሚገኘው የት ነበር?** ብለው ይጠይቁት።
- ልጅዎን በቀጣይ በታሪኩ ውስጥ ምን ሊከሰት እንደሚችል እንዲያስብ እና ታሪኩ የሚካሄድበትን ቦታ ስዕል እንዲስል በማድረግ ይህን ተግባር ማስፋት ይችላሉ።

የጆርናል ሙከራ፥ እኔ የቡድን ተጫዋች ነኝ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የቡድን ተጫዋች የጆርናል ገጽ፣ ከለሮች

- ከልጅዎ ጋር በስፖርት ቡድን ውስጥ፣ በክፍል ውስጥ ወይም በቤት ውስጥም ጭምር ጥሩ የቡድን ተጫዋች መሆኑን ማሳየት ስለሚችልበት ዘዴ በተመለከተ ተነጋገሩ፤ ለምሳሌ፡ የቡድን አባላትን ማዳመጥ፣ መመሪያዎችን መከተል እና ሌሎችን ማበረታታት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ጥሩ የቡድን ተጫዋች ስለመሆን እንዲጽፍና እንዲስል ያድርጉ።
- ከዚያም **እስኪ ጥሩ የቡድን ተጫዋች መሆንህን እንዴት እንደምታሳይ ንገረኝ** ብለው ይጠይቁት።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ ________________

መልካም የቡድን አባል ስለሆናችሁባቸው ጻፉ እንዲሁም ስዕል ሳሉ።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ረቡዕ

STEM: ከ0-4 ቁጥሮችን ማስታወስ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ እያንዳንዱን ከ0-4 ያሉትን ቁጥሮች በቁራጭ ወረቀት ላይ ይጻፉ። ለእያንዳንዱ ቁጥር 2 የቁጥር ካርዶቸ ያዘጋጁ

- ከ3-4 ጥንድ ካርዶች ይምረጡ። ልጅዎን እንዴት የማዛመድ ጌም እንደሚጫወት ያሳዩት። ካርዶቹን ገልብጠው ያስቀምጧቸው። ሁለት ካርዶች ይሳቡ። ቁጥሮቹ የሚዛመዱ ከሆነ ቁጥሮቹን ይጥሯቸውና ከጨዋታው ውስጥ ያውጧቸው። ካርዶቹ የማይዛመዱ ከሆነ መልሰው ገልብጠው ያስቀምጧቸው።
- ከልጅዎ ጋር ተራ ይቀያየሩና ሁሉንም ቁጥሮች እስከምታዛምዱ ድረስ ተጫወቱ።
- ጌሙን የበለጠ ፈታኝ ለማድረግ ተጨማሪ ቁጥሮች ይጨምሩ!

በግል መማር፥ ሜዳሊያዎች መስራት

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለሮች፣ ሪባን ወይም ክር፣ መቀስ

- ልጅዎን አንድ ትልቅ ክብ ቆርጦ እንዲያወጣ ይርዱት።
- ሜዳሊያ ያገኙ ሰዎች እንዴት ስኬታቸውን እንደሚያሳዩ በተመለከተ ተነጋገሩ። የሜዳሊያዎች ምሳሌ ለማሳየት ስልክዎን ወይም ታብሌትዎን ይጠቀሙ።
- ከዚያም **ጥሩ የሆንክባቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?** ብለው ይጠይቁት። ልጅዎን የራሱን ሜዳሊያ እንዲስልና ቀለም እንዲቀባ ያድርጉ።
- ከዚያም የሚዳሊያው ጫፍ ላይ ቀዳዳ ይብሱና በውስጡ ሪባን አሳልፈው ይቋጥሩት። ልጅዎን ሜዳሊያውነ እንዲያጠልቅ ያበረታቱት።
- ልጅዎ በተጨማሪም ለቤተሰብ አባላት ወይም ጓደኞቹ ሜዳሊያዎችን ሊሰራ ይችላል!

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ረቡዕ

እውቀት፥ የቃላት ድምጾችን መቀላቀል

- ለልጅዎ **እስኪ ቃላትን እንቀላቅል! የዚህን ቃል የመጀመሪያና ቀሪ ድምጾችን እቀላቅላለሁ። B-at፣ b-at።** ሁለቱን ክፍሎች በሚቀላቅሉበት ወቅት በፍጥነት ደግመው ይናገሩ። **B-at, bat። ሞክር፣ b-at፣ bat!**
- **አሁን የአንተ ተራ ነው!** ይበሉት። ልጅዎን t-eam (team)፣ s-un (sun)፣ c-up (cup)፣ t-ub (tub) የሚሉትን ቃላት ለመቀላቀል እንዲሞክር ያድርጉ።

ያንብቡ፥ ማክሲሚሊያን/*Maximilian*፣ ትልቁ የአለማችን እጅግ ድንቅ የምግብ ባለሙያ/*The Greatest Most Extraordinary Chef in the World*

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ *ማክሲሚሊያን/Maximilian፣ ትልቁ የአለማችን እጅግ ድንቅ የምግብ ባለሙያ/The Greatest Most Extraordinary Chef in the World*

- ምንባቡን ከልጅዎ ጋር ሆነው ያንብቡ።
- ከዚያም በጋራ ሆናችሁ ማብሰል ስለምትፈልጉት ወይም በጋራ ሆናችሁ መማር ስለምትፈልጉት ልዩ ነገር ተነጋገሩ። ይህን ብዙም ሳይቆይ በጋራ ለማብሰል ማቀድ ትችላላችሁ።



ማክሲሚሊያን፣ ትልቁ የአለማችን እጅግ ድንቅ የምግብ ባለሙያ

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

እስኪ እንንቀሳቀስ፥ የአካል ቋንቋዬን እንደ መስታወት አሳየኝ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከቀን 8 የተወሰደ [**የስሜት ፖስተር**]

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው አካሎቻችን ለሌሎች ሰዎች ምን አይነት ስሜት እየተሰማን እንደሆነ ለማወቅ እንደሚረዷቸው ተነጋገሩ፤ ለምሳሌ፡ ቀዝቀዝ ስንል እንዳዘንን ወይም ወደ ላይና ወደ ታች ስንዘል ስንዘል ደሰተኛ እንደሆንን።
- ከልጅዎ ጋር ሆነው የስሜት ጌም ተጫወቱ። የአካል ቋንቋ ተጠቀሙ፣ ለምሳሌ፡ ደስታችሁን ለማሳየት እጆቻችሁን ከጭንቅላታችሁ በላይ ማወዛወዝ። ልጅዎን ስሜትዎን እንዲገምት ያድርጉ።
- ሚናችሁን ተቀያየሩ።

አንድ ላይ ሆኖ መማር፥ እኛ ቡድን ነን

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ለቡድን ጌማችሁ ወይም ተግባራችሁ በጋራ የምትመርጧቸው ቁሶች

- ለልጅዎ **ቤተሰቦች ብዙ ወይም ትንሽ ሊሆኑ ይችላሉ። አንዳንድ ቤተሰቦች ሁለት ብቻ አባላት ሊኖሯቸው የሚችል ሲሆን ሌሎች ደግሞ ከዚያ በላይ ይኖራቸዋል** ብለው ይንገሩት። ለልጅዎ በተጨማሪም ቤተሰባችሁ አብሮ የሚሰራ፣ የሚተባበር፣ የሚደጋገፍ እና አንዱ አንዱን የሚያበረታታ ቡደን ሊሆን ስለሚችልበት ዘዴ ይንገሩት።
- እንደ ቡድን በጋራ የምትሰሩትን ተግባር ምረጡ። በጋራ የምትጫወቱት የቦርድ ወይም የእንቅስቃሴ ጌሞች ልትመርጡ ትችላላችሁ ወይም እንደ ቁምሳጥን መደርደር ወይም ክፍል መቀባት የመሳሰሉ ተግባሮችን በጋራ ልታጠናቅቁ ትችላላችሁ።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

STEM: የልብ ቱቦዎች

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ንጹህ የጋሎን ጆግ፣ 2 የፕላስቲክ ቱቦዎች ወይም መያዣዎች፣ የመለኪያ ኩባያ፣ ውሀ

- የጋሎን ጆጉን በውሀ ይሙሉና ለልጅዎ ያሳዩት። ከዚያም **ልባችን በደቂቃ አንድ ጋሎን ደም ይረጫል። እስኪ በደቂቃ እንደ ልባችን አንድ ጋሎን ውሀ መርጨት እንደምንችል እንይ** ብለው ይንገሩት።
- ውሀውን ከጋሎን ጆጉ ወደ ውሀ መያዣው ይገልብጡ። ከዚያም **ውሀ ከሙሉ መያዣ ወደ ባዶ የውሀ መያዣ ለመገልበጥ ይህን የመለኪያ ኩባያ ትጠቀማለህ** ብለው ይንገሩት።
- ምርምርዎን ከልጅዎ ጋር ሆነው ያጠናቁ። ከዚያም **ይህ ብዙ ውሀ ነው!** ይበሉት።

በግል መማር፥ በቁጥር ከለር መቀባት

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ [በቁጥር ከለር መቀባት፣](#) ከለሮች

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው እያንዳንዱን ከለሮች ይመልከቷቸው እና እንዴት በቀለም ከለር የመቀባት ተግባሩን እንደሚያጠናቅቅ ያብራሩለት። **1ን ስትመለከት ይህን ቦታ ሀምራዊ ቀለም ቀባ፣ 2ን ስታይ ይህን ቦታ ሰማያዊ ቀለም ቀባ፣ ወዘተ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ስዕሉን እንዲቀባ ያድርጉ።
- ከዚያም **ይህ ምን አይነት ከለር ነው? ስዕሉ ምን እንደሆነ ልትነግረኝ ትችላለህ?** ብለው ይጠይቁት።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ሃሙስ

PK3 ክፍል 11 ሳምንት 4 ቀን 19

እውቀት፥ የታሪክ ክስተቶች

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የትኛውም መጽሀፍ

- ከልጅዎ ጋር ሆነው አጭር መጽሀፍ ያንብቡ። በታሪኩ ውስጥ ስለተከሰቱ ክስተቶች ተነጋገሩ። ከዚያም **ክስተት ማለት የተወሰነ የሚከሰት ነገር ነው። በታሪኩ ውስጥ ምን ተከሰተ?** ብለው ይጠይቁት።
- ክስተቶቹን በድጋሚ ተመልክታችሁ መልሳችሁ ተነጋገሩ። በተጨማሪም ክስተቶቹን አስመስላችሁ ልትተውኑ ትችላላችሁ።
- ይህን ተግባር ልጅዎን በውስጡ ከ2-3 ክስተቶችን የያዘ ታሪክ እንዲጽፍ፣ ወይም ባነበበው ታሪክ ውስጥ ሊከሰት ስለሚችል ስለ ሌላ ክስተት እንዲያስብ በመጠየቅ ማስፋት ይችላሉ።

የጆርናል ሙከራ፥ እኔ እኮራለሁ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ እኔ እኮራለሁ፣ ከለሮች

- ልጅዎን **ማክሲሚሊያን በሚያበስለው ምግብ ይኮራ ነበር። አንተን የሚያኮራህ ነገር ምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት።
- ልጅዎን ስለሚኮራበት ነገር እንዲስልና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ከዚያም **ስለዚህ ለመጻፍና ለመሳል የመረጥከው ለምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት። ማረጋገጫና ማበረታቻ ይስጡት።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።



1 የወይን ጠጅ

2 ሰማያዊ

3 ብርቱካናማ

4 አረንጓዴ

5 ቀይ

6 ቡናማ

7 ቢጫ

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ ________________

ስለምትኮሩበት አንድ ነገር ጻፉ እንዲሁም ስዕል ሳሉ።

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

አርብ

PK3 **ክፍል** 11 **ሳምንት** 4 **ቀን** 20

STEM: ከ5-10 ቁጥሮች የመቆም ዳንስ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ በተለያዩ ቁራጭ ወረቀቶች ላይ ከ5-10 ቁጥሮችን ይጻፉ

- የቁጥር ካርዶቹን ወለል ላይ የተለያዩ ቦታዎች ያስቀምጧቸው።
- ልጅዎን **እስኪ የቁጥር ካርዶቹን በመጠቀም ቀጥ ብሎ የመቆም ዳንስ እንጫወት** ይበሉት። ወለል ላይ ያሉትን ቁጥሮች በጋራ ሆናችሁ ጥሯቸው።
- **ሙዚቃው በሚጫወትበት ወቅት መደነስ ትችላለህ። ሙዚቃው በሚያቆምበት ወቅት እኔ ቁጥር እጠራለሁ። አንተ ቁጥሩን ወለል ላይ ፈልግና ቀጥ ብለህ ቁምበት** ይበሉት።
- ጥቂት ዙሮችን ተጫወቱ። ከዚያም ልጅዎን እንዲመራና ድምጹን ከፍ አድርጎ እርስዎ የሚፈልጉትን ቁጥር እንዲጠራ ያድርጉ።

በግል መማር፥ የምግብ ማውጫ ዝርዝር ማዘጋጀት

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለሮች

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው የምግብ ማውጫ ዝርዝር ከታብሌት ወይም ስልክ ላይ ተመልከቱ፤ ለመመገብ ስለምትሄዱባቸው ቦታዎች የምግብ ማውጫ ዝርዝር ወይም ማክሲሚሊየን ስላዘጋጃቸው ምግቦች ዝርዝር ተነጋገሩ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ የዕለቱን የምግብ ማውጫ ዝርዝር እንዲያዘጋጅ ያድርጉ። ልጅዎ ስዕሎች ቢስል፣ ቢሞነጫጭር ወይም የአጻጻፍ ስህተት ቢፈጥር ምንም ማለት አይደለም!
- ቀጥለውም **በምግብ ማውጫ ዝርዝርህ ውስጥ ምን ምግቦች ወይም ስናኮችተካተዋል?** ብለው ይጠይቁት።
- ከተማቸለ ከምግብ ማውጫ ዝርዝሩ ውስጥ የምታዘጋጇቸውን ከ1-2 ነገሮች ምረጡ።

ልጅዎ እንዴት እንደሚጽፍ በተመለከተ ተጨማሪ ለማወቅ [እዚህ ላይ ያንብቡ።]

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

አርብ

እውቀት፥ የበጋ ወቅት ታሪኬ

- ከልጅዎ ጋር ሆነው ታሪክ ስለመንገር ተለማመዱ። ከዚያም **እስኪ ታሪክ እንነጋገር! እስኪ በዚህ የበጋ ወቅት ስለተከሰተ ነገር ወይም ስለሚከሰት ነገር ንገረኝ** ብለው ይጠይቁት። ልጅዎን ስለ ሁለት ክስተቶች እንዲነግርዎ ያበረታቱት።
- ልጅዎ እርዳታ ካስፈለገው **እስኪ እኛ ... ስላደረግንበት ጊዜ** እና **ምን እንደተከሰተ ንገረኝ?** ብለው ይንገሩት።

*ያንብቡ፥ ማክሲሚሊያን/**Maximilian**፣ ትልቁ የአለማችን እጅግ ድንቅ የምግብ ባለሙያ/**The Greatest Most Extraordinary Chef in the World***

አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ *ማክሲሚሊያን/Maximilian፣ ትልቁ የአለማችን እጅግ ድንቅ የምግብ ባለሙያ/The Greatest Most Extraordinary Chef in the World*

- ምንባቡን ከልጅዎ ጋር ሆነው ያንብቡ።
- ከዚያም **በታሪኩ ውስጥ የጠከሰቱት ሁለት ክስተቶች ምንድን ናቸው?** ብለው ይጠይቁት።



ማክሲሚሊያን፣ ትልቁ የአለማችን እጅግ ድንቅ የምግብ ባለሙያ

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ለልጅዎ እና ለቤተሰብዎ በእንቅስቃሴ እና በበጋ ወቅት መዝናኛ ላይ ትኩረት በሚያደርገው
በአካል ብቃት እንቅስቃሴ ክፍል ለመዝናናት ይዘጋጁ!

AppleTree

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።